## ምዕራብ ፡ ፴፩ ፡ እስያ ።

### የቺን ፡ ነገሥታት ፡ አጭር ፡ ታሪክ ።

፩ ፤ ሻቲ ፡ የተባለው ፡ የቺን ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ በክርስትና ፡ ዘመን ፡ ይኖር ፡ ነበር ። ይኸው ፡ ንጉሥ ፡ ዓለም ፡ እስከታልፍ ፡ እንዲገዛ ፡ ይመኝ ፡ ነበር ። እንዲያውም ፡ ምኞቱ ፡ በጭራሽ ፡ ለዘለዓለም ፡ ገዢ ፡ ሆኖ ፡ እንዲኖር ፡ ነበር ። ስለዚህ ፡ ሕያው ፡ ሆኖ ፡ ለመኖር ፡ እንዲችል ፡ የሚረዳውን ፡ አረቄ ፡ በማውጣት ፡ ዘመኑን ፡ አሳለፈው ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ያልታደለ ፡ አረቄው ፡ ገና ፡ እንደሚገባ ፡ ሆኖ ፡ ሳይደርስ ፡ ንጉሡ ፡ ሞተ ።

፪ ፤ ሌላው ፡ ንጉሥ ፡ ደግሞ ፡ የዜጎቹን ፡ ጉዳይ ፡ ማከናወን ፡ ትቶ ፡ መጽሐፍን ፡ ብቻ ፡ መማር ፡ ወደደ ፡ ( ፈቀደ ) ፡ ጠቅላይ ፡ ሚኒስትሩ ፡ የንጉሡን ፡ ጉዳይ ፡ ሁሉ ፡ ያከናውን ፡ ነበረና ፡ ወዲያው ፡ በንጉሡ ፡ ላይ ፡ ሕዝቡን ፡ አስነሣበት ። ንጉሡም ፡ ጩኸትና ፡ ውካታ ፡ ቢሰማ ፡ መጽሐፉን ፡ አጠፈና ፡ የጦር ፡ መሣሪያውን ፡ ይዞ ፡ ወደከተማው ፡ ተጠግቶ ፡ ቢመለከት ፡ ሁከቱን ፡ ለማቆም ፡ ጊዜው ፡ እንዳለፈ ፡ አስተዋለ ። ወደ ፡ ከተማ ፡ ተመለሰና ፡ መቶ ፡ አርባ ፡ ሺህ ፡ መጻሕፍት ፡ የነበረበትን ፡ የመጻሕፍት ፡ ቤት ፡ በገዛ ፡ እጁ ፡ አቃጠለው ።

፫ ፤ ቺንን ፡ የሚያህል ፡ ሰፊ ፡ መንግሥት ፡ ያጣበት ፡ በነዚህ ፡ መጻሕፍት ፡ ምክንያት ፡ መሆኑን ፡ ንጉሡ ፡ ስለ ፡ ዐወቀ ። እሳት ፡ አንድዶ ፡ በገዛ ፡ እጁ ፡ ኢቃጠላቸውና ፡ የመጻሕፍቱ ፡ ቤቶች ፡ ሁሉ ፡ ተቃጠሉ ። በኋላም ፡ በላዩ ፡ የሸፈቱት ፡ የገዛ ፡ ሕዝቡ ፡ ገደሉት ።

፬ ፤ ሲጉኤን ፡ የተባለው ፡ ንጉሥ ፡ በ፮፻፷ ፡ ክልደት ፡ በኋላ ፡ ነገሠ ። መኖሪያውን ፡ እጅግ ፡ ባማረ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ አደረገ ። ንጉሡ ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ ልጁ ፡ መጣና ፡ የቤተ ፡ መንግሥቱን ፡ ውበትና ፡ ማማር ፡ አይቶ ፡ እጅግ ፡ ተደነቀ ። እንደዚህ ፡ ያለው ፡ መኖሪያ ፡ ለንጉሡ ፡ መታበያና ፡ ለመጥፊያው ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በተቀረ ፡ ለምንም ፡ አይጠቅምም ፡ ብሎ ፡ በግልጽ ፡ ተናገረ ። ይህን ፡ ተናግሮ ፡ ወዲያው ፡ እጅግ ፡ በብዙ ፡ ዋጋ ፡ የተሠራውን ፡ ከተማ ፡ ከነበረበት ፡ እስኪጠፋ ፡ ድረስ ፡ አቃጠለው ።

፭ ፤ ክዋንግያንግ ፡ የተባለ ፡ አንድ ፡ ጀግና ፡ ከስምንት ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ በፊት ፡ ነግሦ ፡ ነበር ። እርሱም ፡ በጠባዩ ፡ በጣም ፡ ገንዘብ ፡ ቆጣቢ ፡ ሰው ፡ ነበር ። ሁለጊዜ ፡ መኝውንም ፡ በንገቱ ፡ ቃጭል ፡ አስሮ ፡ ምንም ፡ ባልተነጠፈበት ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ ይተኛል ፡ እንጂ ፡ ከቶ ፡ ዐልጋ ፡ ላይ ፡ ወጥቶ ፡ መተኛት ፡ አይወድም ፡ ነበር ። እንቅልፍ ፡ ወስዶት ፡ ሳለ ፡ ሲገላበጥ ፡ የቃጭል ፡ ድምጥ ፡ የሰማ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የመነሻው ፡ ጊዜ ፡ የደረሰ ፡ ይመስለው ፡ ነበር ።

፮ ፤ በ፲፪፻፱ ፡ ጀንጊስ ፡ ክሀን ፡ የተባለ ፡ ራስ ፡ የሌለው ፡ የታርታሮችን ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ይዞ ፡ ቺንን ፡ ወረራት ፤ እርሱና ፡ ተወላጆቹ ፡ መላውን ፡ የንጉሠ ፡ ነገ

ሥት ፡ አገር ፡ ድል ፡ አደረጉና ፡ አገሩን ፡ በመላው ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ ሲገዙት ፡ ቆዩ ።

፮ ፡ ከሦስት ፡ ወይም ፡ ካራት ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ በፊት ፡ ችንፃ ፡ ነገሠ ። በዘመኑ ፡ አንድ ፡ ጕድጓድ ፡ ተገኘና ፡ ታላቅ ፡ ዋጋ ፡ ያላቸው ፡ የከበሩ ፡ ድንጋዮች ፡ ተዚያ ፡ ጕድጓድ ፡ እየተቆፈሩ ፡ ይወጡ ፡ ጀመር ። ከነዚሁ ፡ አያሎችን ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ አምጥተው ፡ ቢያሳዩት ፡ በለግጥ ፡ እንጂ ፡ እንደቁም ፡ ነገር ፡ አልተገነዘባቸውም ።

፯ ፡ የከበሩ ፡ ደንጎች ፡ የምትሉዋቸው ፡ እነዚህን ፡ ነውን ፡ ? አለ ። ለምን ፡ ይጠቅማሉ ፡ ? ለሕዝብ ፡ ልብስ ፡ ወይም ፡ ምግብ ፡ አይሆኑ ፡ ጕድጓዱን ፡ መልሳችሁ ፡ ድፈኑት ፡ ሠራተኞቹም ፡ ሌላ ፡ የሚጠቅም ፡ ሥራ ፡ ይሥሩ ፡ አለና ፡ አዘዘ ።

፰ ፡ ከመቶ ፡ ዓመት ፡ በፊት ፡ ዮንግጭንግ ፡ የተባለ ፡ ሰው ፡ በነገሠ ፡ ዘመን ፡ ታይቶ ፡ ያልታወቀ ፡ የሚያስፈራ ፡ ታላቅ ፡ የምድር ፡ መናወጥ ፡ ሆኖ ፡ ነበር ። በፔኪንግ ፡ ከተማ ፡ ያሉ ፡ ቤቶች ፡ ሁሉ ፡ በመናወጽ ፡ ወድቀው ፡ መቶ ፡ ሺህ ፡ ሕዝብ ፡ በውስጥ ፡ ተቀበሩ ። በከተማው ፡ ዙሪያ ፡ ያሉትም ፡ ሳይቀሩ ፡ ብዙ ፡ ሕዝብ ፡ አለቁ ።

፱ ፡ ቺኖች ፡ መቸውንም ፡ ወደ ፡ አገራቸው ፡ ውስጥ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰው ፡ ቢገባባቸው ፡ አይወዱም ። በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ብዙ ፡ ክርክር ፡ እየሆነ ፡ እስከ ፡ ጦርነት ፡ የሚያደርስ ፡ ሆኖዋል ። አሁን ፡ ግን ፡ የውጭ ፡ መንግሥታት ፡ የሚልኩዋቸውን ፡ አምባሳደሮች ፡ በንጉሡ ፡ አደባባይ ፡ ደኅና ፡ አድርገው ፡ የሚቀበሉ ፡ ሁነዋል ። የዛሬው ፡ ሥልጣኔ በመዘርጋቱና ፡ በመንግዱም ፡ መብዛት ፡ ያሁኑ ፡ መለወጥ ፡ ለቺኖች ፡ ታላቅ ፡ ጠቀሜታ ፡ እንዲያመጣላቸውና ፡ በቶሎም ፡ ማግኘታቸውን ፡ አንጠራጠርም ።

## ጥ ያ ቄ ።

፩ ፡ ሻቲ ፡ የተባለው ፡ ንጉሥ ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ? ምን ፡ ሲያደርግ ፡ ኖረ ፡ ?

፪ ፡ እጅግ ፡ ሊቅ ፡ ስለ ፡ ነበረው ፡ ንጉሥ ፡ ተናገር ።

፫ ፡ ሲጉኤን ፡ የነገሠው ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ ? መኖሪያው ፡ የትላይ ፡ ነው ፡ ? ልጁ ፡ ምን ፡ አደረገ ፡ ?

፬ ፡ ክዋንግያንግ ፡ ምን ፡ አደረገ ፡ ? ስለርሱ ፡ ምን ፡ ይነገርለታል ፡ ?

፭ ፡ ጀንጊስ ፡ ካሀን ፡ ቺንን ፡ የወረረው ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ነው ? ስለርሱና ፡ ስለትውልዱ ፡ ምን ፡ ይባላል ፡ ?
ንጉሥ ፡ ቺንፃ ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ? አንድ ፡ የማዕድን ፡ ጕድጓድ ፡ ተገኝቶ ፡ የሆነውን ፡ ተርክ ።
ዮንግጭንግ ፡ በነገሠ ፡ ዘመን ፡ ምን ፡ ሆነ ፡ ?

፱ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ ወደቺን ፡ ለመግባት ፡ በመፈቀዱ ፡ ምን ፡ ተደረገ ፡ ? እንዲህ ፡ በመሆኑ ፡ ምን ፡ (ተደረገ) ይሆናል ፡

## ምዕራፍ ፡ ፴፪ ፡ እስያ ።

### የቻይን ፡ ከተሞች ፡ አኳኋናቸውና ፡ ጠባያቸው ፡ ኑሮአቸውም ።

፩ ፤ የቻይን ፡ ሕዝብና ፡ ከተሞች ፡ በዛሬው ፡ ዘመን ፡ እንዴት ፡ እንደሆኑ ፡ ትንሽ ፡ አሳብ ፡ ልንገራችሁ ። የቻኖች ፡ የቀድሞ ፡ ከተማቸው ፡ ናንኪን ፡ ነበር ። ሁለት ፡ ሚሊዮን ፡ ሕዝብ ፡ ያለበትን ፡ ፔኪን ፡ አሁን ፡ ዋና ፡ ከተማ ፡ አድርገውታል ። የንጉሡ ፡ ዋና ፡ ቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ የተሠራበት ፡ ታርታር ፡ ሲቲ ፡ የሚሉት ፡ በፔኪን ፡ ክፍል ፡ ነው ።

፪ ፤ የፔኪን ፡ ግንብ ፡ የተሠራው ፡ በጡብ ፡ ነው ። ከፍታው ፡ መቶ ፡ ፊት ፡ ስለሆነ ፡ መላውን ፡ ከተማ ፡ ሊሰውረው ፡ ይችላል ። ወፍራም ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ዘበኞች ፡ በፈረስ ፡ እንደ ፡ ተቀመጡ ፡ በግንቡ ፡ ጫፍ ፡ ላይ ፡ በከተማው ፡ ዙሪያ ፡ ሊጋልቡ ፡ ይችላሉ ። በዕብነ ፡ በረድ ፡ እየተቀሰቱ ፡ የተሠሩ ፡ ርዝመታቸው ፡ እጅግ ፡ ታላቅ ፡ የሆኑ ፡ ዘጠኝ ፡ በሮች ፡ አሉት ።

፫ ፤ የቻይን ፡ ሕዝብ ፡ መልካቸው ፡ እንደ ፡ ዘይት ፡ መልክ ፡ ጠየም ፡ ያሉ ፡ ሆነው ፡ ጠጕራቸው ፡ ጥቍር ፡ ዐይነ ፡ ትንንሾች ፡ ናቸው ። ልብሳቸው ፡ ሰፊ ፡ ረጅም ፡ ቀሚስ ፡ ነው ። ከሐር ፡ በተሠራ ፡ መታጠቂያ ፡ ሸብ ፡ ያደርጉታል ። በዚህ ፡ መታጠቂያ ፡ ማንካና ፡ አንድ ፡ ካራ ፡ በሹካ ፡ ፈንታ ፡ ለመብሊያቸው ፡ ሁለት ፡ ዕንጨት ፡ ይይዛሉ ።

፬ ፤ ቻኖች ፡ በእጅ ፡ ሥራ ፡ በጣም ፡ የታወቁ ፡ ናቸው ። ስኒያቸውና ፡ ሸክላቸው ፡ ከዝሆን ፡ ጥርስ ፡ የተሠራ ፡ ካራቸውና ፡ የኩክ ፡ ማውጫቸው ፡ የዕንቍ ፡ ብዛት ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ በኤውሮጳ ፡ ታውቆዋል ። ከሌላው ፡ ሁሉ ፡ ይልቅ ፡ የግብርና ፡ ሥራ ፡ በጣም ፡ የተለመደ ፡ ነው ። ትንሽቱ ፡ ስፍራ ፡ ሁሉ ፡ ሳትቀር ፡ ታርሳለች ። ዋናው ፡ በገሩ ፡ የሚገኘው ፡ ሩዝና ፡ ሻይ ፡ ነው ።

፭ ፤ በገሩ ፡ ውስጥ ፡ ወርቅና ፡ ብር ፡ በየስፍራው ፡ ይገኛል ። በተራራው ፡ ላይ ፡ ይልቁንም ፡ በሰሜንና ፡ በምዕራብ ፡ ብረትና ፡ መዳብ ፤ ባዚቃ ፤ ዕብነ ፡ በረድ ፤ የድንጋይ ፡ ከሰል ፤ የክርስታል ፡ ደንጊያና ፡ ያስጴር ፡ ይገኛል ።

፮ ፤ የቻይን ፡ ወይዛዝሮች ፡ በጫማቸው ፡ ማነስ ፡ በጣም ፡ የታወቁ ፡ ናቸው ። የቻይን ፡ ትልቅ ፡ የተባለችው ፡ ሴት ፡ የምትሰከው ፡ ጫማ ፡ የኤውሮጳ ፡ ትንሽቱ ፡ ልጅ ፡ ከምታደርገው ፡ ጫማ ፡ ያንሳል ። ጫሞቻቸው ፡ እንዲያው ፡ ለዐይን ፡ ነው ። እንጂ ፡ ለመሄጃ ፡ ከቶ ፡ አይጠቀሙም ።

፯ ፤ ሃይማኖት ፡ በቻኖች ፡ መኻከል ፡ ያለው ፡ በሚያሳዝን ፡ ሁኔታ ፡ ነው ። ሕዝቡ ፡ ጣዖት ፡ ለማምለክ ፡ የተሰጡ ፡ ናቸው ። ሃይማኖት ፡ ሁሉ ፡ አይከለከልም ። ማንኛውንም ቢሆን ፡ የሚያከብሩት ፡ በጥቂቱ ፡ ነው ። ለቍጥር ፡ የሚያሳስቱ ፡ አብያተ ፡ ጣዖታት ፡ ተሠርተዋል ።

፰ ፡ በቺን፡አገር ፡ ማንም ፡ ሚስት ፡ ለማግባት ፡ ቢፈልግ ፡ ካባትና ፡ ከናቱዋ ፡ ይገዛል ። ነገር ፡ ግን ፡ ከቤቱ ፡ ካልደረሰች ፡ ለማየት ፡ አይፈቀድለትም ። ሙሽራዪቱ ፡ በመጋረጃ ፡ እንደ ፡ ተሸፈነች ፡ ወደባልዋ ፡ ቤት ፡ በደረሰች ፡ ጊዜ ፡ ሙሽራው ፡ መጋረጃውን ፡ ገልጦ ፡ ወደሙሽራዪቱ ፡ አሾልቆ ፡ ይመለከትና ፡ መልክዋ ፡ ደስ ፡ ሳያሰኘው ፡ የቀረ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወደ ፡ ቤትዋ ፡ ይመልሳታል ።

፱ ፡ በቺን፡አገር ፡ እንደዚህ ፡ ያሉ ፡ መቀጫዎች ፡ አሉ ። ሁለት ፡ ፓውንድ ፡ የሚመዝን ፡ ከዕንጨት ፡ የተሠራ ፡ ነገር ፡ አላቸው ። ያንን ፡ በሰውዬው ፡ አንገት ፡ ያገቡበትና ፡ ያንን ፡ እንደ ፡ ተሸከመ ፡ ወደ ፡ ፈቀደው ፡ ስፍራ ፡ ይሄዳል ። ነገር ፡ ግን ፡ ይህ ፡ ነገር ፡ ባንገቱ ፡ እስከ ፡ አለ ፡ ድረስ ፡ ሊበላ ፡ ወይም ፡ ሊተኛ ፡ አይችልም ።

፲ ፡ ቺኖች ፡ ደግሞ ፡ አንድ ፡ ልዩ ፡ ልማድ ፡ አላቸው ። ይህም ፡ ልማድ ፡ የውጭ ፡ ሰው ፡ ወደ ፡ አገራቸው ፡ ውስጥ ፡ እንዳይገባ ፡ ዘግተው ፡ መከልከላቸው ፡ ነው ። በኋላ ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ ካንቶን ፡ በሚባል ፡ ስፍራ ፡ ጥቂቶች ፡ አውሮጳችና ፡ ያሜሪካ ፡ ነጋዴዎች ፡ ብቻ ፡ ሚስቶቻቸውን ፡ በማከዎ ፡ እየተዉ ፡ እነሱ ፡ እንዲገቡ ፡ ፈቀዱላቸው ። በተቀረ ፡ ማንም ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰው ፡ ወደ ፡ አገራቸው ፡ እንዲገባ ፡ አልተፈቀደም ። አሁን ፡ ግን ፡ ለውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ ንግዳቸውን ፡ የሚነግዱበት ፡ ፳ ፡ ስፍራዎች ፡ ሰጥተዋቸው ፡ በዚያ ፡ ሁነው ፡ እንዲነግዱ ፡ ተፈቅዶላቸዋል ። ቺኖች ፡ እንደሚያስቡት ፡ ደንባቸውና ፡ ልማዳቸው ፡ ከዓለም ፡ ሁሉ ፡ የነርሱ ፡ የተሻለ ፡ ስለ ፡ መሰላቸው ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ ወደ ፡ አገራቸው ፡ ገብተው ፡ ሌላ ፡ አሳብ ፡ ሊያገቡ ፡ አይወዱም ። እነሱ ፡ ጥንታዊ ፡ ሕዝብ ፡ ናቸው ። ይኸንኑ ፡ የጥንት ፡ ልማዳቸውን ፡ መጠበቅ ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡ መጨመር ፡ የማይፈልጉ ፡ ናቸው ።

፲፩ ፡ ቺን ፡ አያሌ ፡ ታላላቅ ፡ ሰፋፊ ፡ ከተሞች ፡ አሉት ። በነዚህም ፡ ከተሞች ፡ ውስጥ ፡ ስፍር ፡ ቍጥር ፡ የሌላቸው ፡ ሕዝብ ፡ ይኖሩባቸዋል ። የባሕርይ ፡ ዕውቀትና ፡ የጅ ፡ ሥራም ፡ ዕውቀት ፡ አላቸው ። እርሻቸውንም ፡ የሚያርሱት ፡ በታላቅ ፡ ብልሀት ፡ ነው ። አታክልታቸውንም ፡ የሚሠሩ ፡ በተለየ ፡ ጥንቃቄ ፡ ነው ።

፲፪ ፡ ሻይ ፡ ሌላም ፡ ብዙ ፡ ልዩ ፡ ዕቃ ፡ የሚመጣልን ፡ ከዚህ ፡ አገር ፡ ነው ። የሕዝቡ ፡ ብዛት ፡ ከሦስት ፡ መቶ ፡ ፹ ፡ ሁለት ፡ ሚሊዮን ፡ ይበዛሉ ።

## ጥ ያ ቄ ።

፩ ፡ የቀድሞ ፡ የቺን ፡ ዋና ፡ ከተማ ፡ ማን ፡ ነበር ፡ ? የዛሬውስ ፡ ማነው ፡ ?
በፔኪንግ ፡ የባላገሮቹ ፡ ቍጥር ፡ ስንት ፡ ይሆን ፡ ?
የንጉሡ ፡ መኖሪያ ፡ ወዴት ፡ ነው ፡ ?

፪ ፡ የፔኪንግ ፡ ግንብ ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ነው ፡ ?
በሩ ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ነው ፡ ?

፫ ፡ የቺን ፡ ሕዝብ ፡ እንዴት ፡ ያሉ ፡ ናቸው ፡ ? ልብሳቸው ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ነው ፡ ?

፬ ፡ ስለ ፡ ሥራቸው ፡ ተናገር ።

፭ ፤ ዋናው ፡ ማዕድን ፡ ምንድን ፡ ነው ፡ ?
፮ ፤ የቺን ፡ ሴቶች ፡ እንዴት ፡ ያሉ ፡ ናቸው ፡ ?
፯ ፤ የቺኖች ፡ ሃይማኖትና ፡ አምልኮት ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ?
ቤተ ፡ ጣዖታቸው ፡ እንደምን ፡ ያለ ፡ ነው ፡ ?
፰ ፤ ሰው ፡ ሚስት ፡ ለማግባት ፡ በፈለገ ፡ ጊዜ ፡ እንዴት ፡ ያደርጋል ፡ ?
፱ ፤ በቺን ፡ ቅጣታቸው ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ?
፲ ፤ ስለ ፡ ውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ልማድ ፡ አላቸው ፡ ?
የነጋዶች ፡ ሚስቶች ፡ ወዴት ፡ ይኖራሉ ፡ ?
ቺኖች ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ ባገራቸው ፡ ውስጥ ፡ እንዳይገቡ ፡ መከልከ
ላቸው ፡ ለምንድነው ፡ ?
በዓለም ፡ የጥንት ፡ መንግሥት ፡ የተባለ ፡ ማነው ፡ ?
፲፩ ፤ የቺን ፡ ከተሞች ፡ እነማን ፡ ይባላሉ ፡ ?
የእጅ ፡ ሥራ ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ?
ሕዝቡ ፡ የግብርና ፡ ሥራ ፡ ያውቃሉን ፡ ?
፲፪ ፤ ሻይ ፡ የምናገኘው ፡ ከወዴት ፡ ነው ፡ ?
በቺን ፡ የሕዝብ ፡ ብዛት ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ?

## ምዕራፍ ፡ ፴፫ ፡ እስያ ።

### የዐረቦች ፡ መጀመሪያ ፡ የሙሐመድ ፡ መንግሥት ።

፩ ፤ ዐረቦች ፡ የአብርሃም ፡ ልጅ ፡ የእስማኤል ፡ ልጆች ፡ (ዘሮች ፡) ናቸው ። እጁ ፡ በሰው ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ እንዲሆን ፡ የሰውም ፡ ሁሉ ፡ እጅ ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ እንዲሆን ፡ አስቀድሞ ፡ ተነግሮለታል ። በሰው ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ ጠላት ፡ መስለው ፡ ስለ ፡ ታዩ ፡ ሰውም ፡ ሁሉ ፡ በነርሱ ፡ ላይ ፡ ጠላት ፡ መስሎ ፡ ስለ ፡ ታየ ፡ ይህ ፡ ትንቢት ፡ በዘመኑ ፡ ሁሉ ፡ በልጆቹ ፡ ላይ ፡ ተፈጸመ ።

፪ ፤ ዐረብ ፡ ሲባል ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የተከፋፈለ ፡ አውራጃና ፡ ነገድ ፡ ነው ። አገሩ ፡ በሰሜን ፡ በኩል ፡ ከጳለስቲናና ፡ ከሚሶጶታሚያ ፤ በምሥራቅ ፡ ወገንም ፡ ከፋርስና ፡ ከአርሙዝ ፡ ባሕር ፤ በደቡብ ፡ ወገን ፡ ከህንድ ፡ ውቅያኖስ ፤ በምዕራብ ፡ ወገን ፡ ከቀይ ፡ ባሕር ፡ ይዋሰናል ።

፫ ፤ ዐረቦች ፡ መቸውንም ፡ በዙረት ፡ የሚኖሩ ፡ ነገድ ፡ ናቸው ። መተላለፊያ ፡ መንገድ ፡ በሌለው ፡ በውድማና ፡ በበረሃ ፡ ውስጥ ፡ በድንኳን ፡ መኖር ፡ ይችላሉ ። የጥንት ፡ ታሪካቸው ፡ ያልተጨረሰ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ታውቆአል ። መቸም ፡ መጀመሪያ ፡ የሆነው ፡ ወሬ ፡ ከውስጣቸው ፡ የሙሐመድ ፡ መወለድ ፡ ነው ። ይህም ፡ የሆነው ፡ በመካ ፡ ከተማ ፡ በቀይ ፡ ባሕር ፡ አጠገብ ፡ በዘመነ ፡ ክርስትና ፡ ፭፻፸ ፡ ዓመት ፡ ነው ።

፩ ፤ ሙሐመድ፡፳፭፡ዓመት፡እስኪሆነው፡በበረሃ፡ግመል፡ነጂ፡ነበር። ከዚህ፡በኋላ፡ የሚበልጠውን፡ጊዜውን፡በብቸኝነት፡(በብሕትውና፡)አሳለፈው፤ መኖሪያው፡ በተለየ፡ዋሻ፡እጸልያለሁ፡በሚልበት፡ስፍራ፡ነው፤ አርባ፡ዓመት፡በሆነው፡ጊዜ፡ ነቢይ፡ነኝ፡ብሎ፡ተነሣ።

፪ ፤ ዓለም፡አዲሱን፡ሃይማኖት፡እንድትቀበል፡ከእግዚአብሔር፡ተልኬአለሁ፡ብሎ፡ ነቢይነቱን፡በግልጽ፡ዐወጀ። የመካ፡ሕዝብ፡መጀመሪያ፡ሙሐመድን፡አላመኑ ትም። ያላመኑበት፡ምክንያትም፡መጀመሪያ፡የተወለደው፡በመካከላቸው፡ነው። ሁለተኛ፡ግመል፡ሲነዳ፡እንደ፡ኖረ፡ያውቃሉ። ሦስተኛ፡ከኛ፡የበለጠ፡ቅዱ ስነት፡ከወዴት፡አመጣ፡? እያሉ፡ነው። ደግሞ፡ከመልአኩ፡ከገብርኤል፡ጋር፡ ሆኜ፡ባህያ፡ተቀምጬ፡ወደ፡ሰማይ፡ጋልቤ፡ሄጄ፡ነበር፡እያለ፡ይነግራቸው፡ ነበር። ማንኛውም፡የሚያመጣው፡ታሪክ፡እንደዚህ፡የመሰለ፡የሚያሥቅ፡ነበር።

፫ ፤ የመካ፡ሕዝብ፡ሙሐመድን፡ሊገድሉት፡ስላ፡አስፈራሩት፡መዲና፡ወደ፡ተባ ለች፡ወደ፡ሌላ፡የዐረብ፡ከተማ፡ሸሽቶ፡ሄደ። ሽሽቱን፡ዐረቦች፡«ሒጅራ፡ በመዲና፡» ይሉታል። በሁለትና፡በሦስት፡ዓመት፡እያሉች፡ሃይማኖቱን፡ተቀ በሉት። ይህን፡ሃይማኖት፡ሌሎችም፡በግድ፡እንዲቀበሉ፡አድርጉዋቸው፡ብሎ፡ ለደቀ፡መዛሙርቱ፡ነገራቸው። እነሱ፡ግን፡ሰውን፡በግድ፡አናስገድድም፡ አሉት።

፬ ፤ ይህም፡በሙሐመድ፡ተማሮችና፡በሌሎች፡ዐረቦች፡መካከል፡ጦርነትን፡አስ ነሣ። በዚህም፡ጦርነት፡ሙሐመድ፡ብዙ፡ጊዜ፡ድል፡አደረገና፡የመላው፡ የዐረብ፡አገር፡ጌታ፡ሆነ። አልፎም፡ሶርያን፡ሁሉ፡ያዘው።

፭ ፤ ሙሐመድ፡በውነት፡ንጉሥ፡ይባል፡ነበር፡እንጂ፡ነቢይ፡ብቻ፡አልተ ባለም። እጅግ፡የሚያስፈራ፡ሰው፡ነበር። ይልቁንም፡የሚከተሉትን፡በተ ቂጣ፡ቍጥር፡በቅንድቡና፡በቅንድቡ፡መካከል፡የደም፡ሥሩ፡ያብጥና፡ይጠ ቍራል። እንዲህ፡በመሆኑ፡በሚያስፈራ፡ሁኔታ፡ይታያል።

፮ ፤ ኅይሉ፡እየበረታ፡ይሄድ፡ነበር። ነገር፡ግን፡ዕድሜው፡፷፫፡ዓመት፡ሲሆ ነው፡በድንገት፡ሞተና፡በመዲና፡ተቀበረ። የተቀበረበት፡ሣጥን፡እስከ፡ዛሬ፡ በመስጊድ፡ይታያል፡ይባላል። አንዳንዶች፡ግን፡ማግኒት፡በሚስብ፡ብረት፡ በዓየር፡ላይ፡ተንጠልጥሏል፡ብለው፡በስንፍና፡ያምናሉ። ስፍራውን፡ለማ የት፡ብለው፡አያሎች፡ጽድቅ፡ፈላጊዎች፡በየዓመቱ፡እየሄዱ፡ይጐበኛሉ።

፯ ፤ የሙሐመድ፡ሃይማኖት፡በእስያና፡በአፍሪካ፡ተዘርግቶአል። ብዙ፡ሚሊዮን፡ ሕዝብ፡አምኖ፡ተቀብሎታል። ሕጉና፡ትእዛዛቱ፡ቍራን፡በሚባለው፡መጽ ሐፍ፡ተጽፎዋል። በዚህ፡መጽሐፍ፡የተጻፈውን፡ትምህርት፡መልአኩ፡ገብ ርኤል፡ከሰማይ፡አመጣልኝ፡ሲል፡ሙሐመድ፡ነገሩን፡አጠነከረ።

፲፩ ፤ ሙሐመድ ፣ ከሞተ ፣ በኋላ ፣ ወራሹ ፣ ማን ፣ እንደሚሆን ፣ ወይስ ፣ ለማን ፣ እንደ ሚገባው ፣ በማለት ፣ ተከታዮቹ ፣ ወደ ፣ መለያየት ፣ ደረሱ ። አንደኛው ፣ ክፍል ፣ ዛሬ ፣ በቱርክ ፣ አገር ፣ የሚኖሩት ፣ ወራሽነት ፣ የሚገባው ፣ ለከሊፍ ፣ ኡመር ፣ ነው ፣ ብለው ፣ ያምናሉ ። እነርሱም ፣ ስኒሽ ፣ ይባላሉ ። ሌሎች ፣ ክፍሎች ፤ ወይም ፣ በፋርስ ፣ የሚኖሩት ፤ ደግሞ ፣ የሙሐመድ ፣ ወራሽ ፣ መሆን ፣ የሚገባው ፣ ከሊፍ ፣ ዓሊ ፣ ነው ፣ ብለው ፣ ያምናሉ ። መሸድ ፣ ዓሊ ፣ በምትባል ፣ በኤፍራጥስ ፣ ወንዝ ፣ አጠገብ ፣ መቃብሩን ፣ ያከብራሉ ። ሺዩስ ፣ ይባላሉ ፤ እነዚህም ፣ የተለያዩ ፣ ሰዎች ፣ ርስ ፣ በርሳቸው ፣ አይፋቀሩም ።

## ጥ ያ ቄ ።

፩ ፤ ዐረቦች ፣ ትውልዳቸው ፣ ከወዴት ፣ ነው ፣ ?
ስለ ፣ እስማኤል ፣ የተነገረው ፣ ትንቢት ፣ እንዴት ፣ ነው ፣ ? ትንቢቱ ፣ ተፈጸመን ፣ ?
፪ ፤ የዐረብ ፣ አገር ፣ ሁኔታ ፣ እንዴት ፣ ነው ፣ ? ዳርቻው ፣ እስከ ፣ የት ፣ ነው ፣ ?
የዐረቦች ፣ አኑዋኑዋር ፣ እንዴት ፣ ነው ፣ ? ከጥንት ፣ ታሪካቸው ፣ እንዴት ፣ ነው ፣ ? ሙሐመድ ፣ ከወዴት ፣ ተወለደ ፣ ?
፫ ፤ ሙሐመድ ፣ ሥራው ፣ ምንድን ፣ ኑሩዋል ፣ ?
፬ ፤ አርባ ፣ ዓመት ፣ ሳይሆነው ፣ እንዴት ፣ ይኖር ፣ ነበር ፣ ? ከዚያ ፣ በኋላ ፣ ምን ፣ አደረገ ፣ ?
የመካ ፣ ሕዝብ ፣ እንዴት ፣ ኑረዋል ፣ ?
ሙሐመድ ፣ ምን ፣ ይል ፣ ነበር ፣ ?
፭ ፤ ሙሐመድ ፣ ወደ ፣ መዲና ፣ ለምን ፤ ሸሸ ፣ ?
የሙሐመድን ፣ መሸሽ ፣ ዐረቦች ፣ ምን ፣ ይሉታል ፣ ?
በመዲና ፣ ሃይማኖቱን ፣ እንዲቀበሉት ፣ ምን ፣ አደረገ ፣ ?
፮ ፤ በዚህ ፣ የተነሣ ፣ ምን ፣ ሆነ ፣ ?
ሙሐመድ ፣ እንዴት ፣ ያለ ፣ ድል ፣ አገኘ ፣ ?
፯ ፤ ሙሐመድ ፣ እንዴት ፣ ያለ ፣ ሰው ፣ እንደ ፣ ነበረ ፣ ትገልጻለህን ፣ ?
፰ ፣ ምን ፣ ጊዜ ፣ ሞተ ፣ ?
ወዴት ፣ ተቀበረ ፣ ?
ስለ ፣ ተቀበረበት ፣ ሣጥን ፣ ምን ፣ ይባላል ፣ ?
፲ ፤ የሙሐመድ ፣ ሃይማኖት ፣ በየት ፣ አገር ፣ ተዘረጋ ፣ ?
ቍራን ፣ ምንድነው ፣ ?
ሙሐመድ ፣ ያጸናው ፣ ነገር ፣ ምንድነው ፣ ?
መካ ፣ ወዴት ፣ ነው ፣ ?
መዲና ፣ ወዴት ፣ ነው ፣ ?
፲፩ ፤ የሙሐመድ ፣ ወራሾች ፣ እነማናቸው ፣ ?
የኡመር ፣ ተከታዮች ፣ እነማናቸው ፤ ?
በዓሊ ፣ ያመኑት ፣ ምን ፣ ይባላሉ ፣ ? እርሱ ፣ ወዴት ፣ ተቀበረ ፣ ?

## ምዕራፍ ፡ ፴፬ ፡ እስያ ።

### ሳራሲን ፡ የተባሉ ፡ ዐረቦች ፡ ታሪክ ፡ ይከታተላል ።

፩ ፡ ሙሐመድን ፡ ከተከተሉት ፡ ወገን ፡ ያሉት ፡ ዐረቦች ፡ ሳራሲን ፡ ይባላሉ ። መሪያ
ቸው ፡ ሙሐመድ ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ በእስያ ፡ ያለውን ፡ ቱርክና ፡ ሌሎችንም ፡ አገ
ሮች ፡ ድል ፡ እያረጉ ፡ ያዙ ። የመንግሥታቸው ፡ ዋና ፡ ከተማ ፡ ባግዳድ ፡ ትባላለች ።
አስቀድሜ ፡ እንደተናገርሁት ፡ ይህች ፡ ከተማ ፡ የተሠራች ፡ በጤግሮስ ፡ ወንዝ ፡
ላይ ፡ ነው ።
፪ ፡ ፊት ፡ እንዳልሁት ፡ ከሙሐመድ ፡ ወራሾች ፡ አንዱ ፡ ዓሊ ፡ ነው ። እርሱም ፡ የወ
ንድሙ ፡ ልጅ ፡ ነው ፤ ይህንንም ፡ የሙዋቹ ፡ የሙሐመድ ፡ ሚስት ፡ አዬሳ ፡ ባል
ዋን ፡ እንደ ፡ ገደለ ፡ ትጠረጥረው ፡ ነበርና ፡ ተጣላችው ።
፫ ፡ ጦር ፡ ሰብስባ ፡ ዓሊን ፡ ለመውጋት ፡ ተነሣች ። ሲዋጉ ፡ ሳሉ ፡ አዬሳ ፡ እንደ ፡ ጥላ ፡
መሳይ ፡ ተደርጎላት ፡ በግመል ፡ ላይ ፡ ተቀምጣ ፡ ነበረች ። የግመሊቱን ፡ ልጓም
አንድ ፡ ወታደር ፡ ይዞ ፡ ቁሞ ፡ ነበርና ፡ በዚያ ፡ ስትመለከት ፡ ሳለች ፡ ሰባ ፡ የሚሆኑ ፡
ወታደሮችዋ ፡ ተገደሉ ፡ ይባላል ። በመጨረሻው ፡ ዓሊ ፡ ድል ፡ አደረገና ፡ የሙሐ
መድ ፡ ተማሮች ፡ ድል ፡ ያደረጉትን ፡ አገር ፡ ሁሉ ፡ ያዘና ፡ በላያቸው ፡ ዋና ፡ ሆነ ።
፬ ፡ የሳራሲን ፡ መንግሥት ፡ እንዲህ ፡ ሆኖ ፡ ተመሠረተ ። ነገሥታቱ ፡ ከሊፎች ፡ ይባ
ላሉ ። በ፲፻፳ ፡ ዓመት ፡ ስሙ ፡ ጥሩው ፡ የጋዚን ፡ ማሕሙድ ፡ የተባለ ፡ በባግዳድ ፡
ነገሠ ። እርሱም ፡ ታላቅ ፡ አሸናፊ ፡ ይባል ፡ ነበርና ፡ የህንድን ፡ ክፍል ፡ ተግዘቱ ፡
አደባልቆ ፡ ገዝቶታል ።
፭ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ መጣና ፡ አንድ ፡ ወታደር ፡ ወደ ፡ ቤቴ ፡ መጥቶ ፡ ‹እኔ
ንና ፡ ቤተ ፡ ሰቤን ፡ ከገዛ ፡ ቤቴ ፡ አስወጥቶ ፡ ገንዘቤን ፡ ሁሉ ፡ ይዞ ፡ በቤቴ ፡ እሱ
ገባበት ፡ እኔ ፡ ከነኝዜ ፡ በውጭ ፡ አደርሁ ፡ ብሎ› ለጋዚኒ ፡ ማሕሙድ ፡ አቤቱታውን
አቀረበ ። ንጉሡ ፡ ማሕሙድ ፡ ይህን ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ምን ፡ አልባት ፡ ይህ ፡
ወታደር ፡ የሚለው ፡ እንዲህ ፡ የሚያደርግ ፡ የገዛ ፡ ልጄ ፡ ይሆናል ፡ ብሎ ፡ ጥር
ጥር ፡ ገባው ። ዳግመኛ ፡ እንዲህ ፡ የበደለህ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ተመልሰህ ፡ እንድትነ
ግረኝ ፡ አለው ።
፮ ፡ እንዲሁ ፡ ዋሶ ፡ አደረና ፡ እንደ ፡ ገና ፡ መጥቶ ፡ ለንጉሡ ፡ ‹ያው ፡ የቀድሞው ፡
ወታደር ፡ መጥቶ ፡ ተቤቴ ፡ አስወጣኝ› ፡ አለው ። ንጉሡም ፡ ሰይፉን ፡ ታጥቆ ፡
ወደ ፡ ሰውዮው ፡ ቤት ፡ ሔደና ፡ ወደ ፡ ቤት ፡ ከመግባቱ ፡ በፊት ፡ መብራቱን ፡ ሁሉ ፡
አጥፉ ፡ ብሎ ፡ አዘዘ ። ይህን ፡ ማለቱ ፡ በደለኛው ፡ ሲቀጣ ፡ በማየት ፡ ልቡ ፡ እን
ዳይራራ ፡ ነበር ።
፯ ፡ መብራቱ ፡ ሁሉ ፡ ጠፋና ፡ ወደ ፡ ቤት ፡ ገብቶ ፡ ወታደሩን ፡ በሰይፍ ፡ ከመታው
በኋላ ፡ መብራት ፡ እንዲበራ ፡ አዘዘ ። እንዲሁምን ፡ አሽከሩ ፡ ባበራለት ፡ ጊዜ ፣

የጋዚኒ ፡ ማሕሙድ ፡ መብራቱን ፡ ይዞ ፡ የወታደሩን ፡ ሬሳ ፡ ቢመለከት ፡ ጥርጣሬው ፡ ከንቱ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አገኘው ፤ የተገደለው ፡ የገዛ ፡ ልጁ ፡ ሳይሆን ፡ ቀረ ።

፰ ፤ በኋላ ፡ የነገሠው ፡ ሞስታስም ፡ ይባላል ። እርሱም ፡ በትዕቢት ፡ የተነፋ ፡ ከንቱ ፡ ክብርን ፡ ፈላጊ ፡ ሰው ፡ ነበር ። እንዲያውም ፡ የገዛ ፡ ሕዝቡን ፡ ቀና ፡ ብላችሁ ፡ ፊቴን ፡ አትመልከቱ ፡ ይል ፡ ነበር ። ስለዚህ ፡ ከወርቅ ፡ የተሠራ ፡ ዓይነ ፡ ርግብ ፡ ከፊቱ ፡ ላይ ፡ ሳያደርግ ፡ አደባባይ ፡ አይወጣም ፡ ነበር ። ወደ ፡ ሜዳ ፡ ወጥቶ ፡ በጋለበ ፡ ቍጥር ፡ ብዙ ፡ ሺሖች ፡ የሚሆኑ ፡ ሕዝብ ፡ በዓይነ ፡ ርግብ ፡ የተሸፈነ ፡ ፊቱን ፡ ለማየት ፡ እንደማይታወቅበቸው ፡ ስርቅ ፡ አድርገው ፡ ያዩታል ፡ እንጂ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ የሚያየው ፡ አንድም ፡ ሰው ፡ አይገኝም ።

፱ ፤ ቀጥሎ ፡ ወዲያው ፡ ሁላኩ ፡ የተባለ ፡ የታርታሮች ፡ አለቃ ፡ የባግዳድን ፡ ከተማ ፡ ያዘ ። የንጉሡን ፡ የሞስታስምን ፡ የወርቅ ፡ ዓይነ ፡ ርግብ ፡ ገፈፈና ፡ ጣለው ። ንጉሡን ፡ ከነነፍሱ ፡ በስልቻ ፡ ውስጥ ፡ አግብቶ ፡ ከተተው ። ቀድሞ ፡ ሲነግሥ ፡ እልልታና ፡ ታላቅ ፡ ልዕልና ፡ ባሳየበት ፡ ጐዳና ፡ ላይ ፡ በስልቻ ፡ እንደ ፡ ተከተተ ፡ በፈረስ ፡ አስጐተተው ።

፲ ፤ ከሊፍ ፡ ሞስታስም ፡ እንዲህ ፡ በአስፋልት ፡ በተሠራ ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡ ተቀጥቅጦ ፡ ሞተ ፤ በዘመነ ፡ ክርስትና ፡ ባ፲፪፻፶፰ ፡ የሳራሲን ፡ መንግሥት ፡ ከርሱ ፡ ጋር ፡ ተጨረሰ ።

፲፩ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ የዚህ ፡ መንግሥት ፡ መፈጸም ፡ የሙሐመድን ፡ ሃይማኖት ፡ አላገደውም ። እንዲያውም ፡ አብልጦ ፡ እየገነነ ፡ ተንሰራፍቶ ፡ በእስያና ፡ በአፍሪካ ፡ በብዙ ፡ አገሮች ፡ ተዘርግቶ ፡ ቀረ ።

## ጥ ያ ቄ ።

፩ ፤ ሳራሲን ፡ የተባሉ ፡ እነማናቸው ፡ ? ስለነርሱ ፡ ምን ፡ ይነገራል ፡ ? የመንግሥታቸው ፡ ዋና ፡ ከተማ ፡ ማን ፡ ይባላል ፡ ?

፪ ፤ ዓሊ ፡ ማነው ፡ ? የነቀፈው ፡ ማነው ፡ ? አዩሳ ፡ ማነው ፡ ?

፫ ፤ በዓሊና ፡ በአዩሳ ፡ መካከል ፡ የነበረውን ፡ ግጭት ፡ ተናገር ። የትኛው ፡ ድል ፡ አደረገ ፡ ?

ከሊፎች ፡ የተባሉት ፡ ወገኖች ፡ እነማናቸው ፡ ? የነገሡበት ፡ የት ፡ ነው ፡ ?

፭ ፤ የጋዚኒ ፡ ማሕሙድ ፡ የተባለው ፡ ማነው ፡ ? የጋዚኒን ፡ ማሕሙድና ፡ የምስኪኑን ፡ ሰውዬ ፡ ታሪክ ፡ ተርክ ።

፮ ፤ ሞስታስም ፡ የተባለው ፡ ማነው ፡ ? ስለርሱ ፡ ምን ፡ ትላለህ ፡ ?

፯ ፤ እንደምን ፡ ሞተ ፡ ?

፲ ፤ የሳራሲን ፡ መንግሥት ፡ የተፈጸመው ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ ?

፲፩ ሰለ ፡ ሙሐመድ ፡ ሃይማኖት ፡ እንደምን ፡ ተደረገ ?

## ምዕራፍ ፡ ፴፰ ፡ እስያ ።

### ስለ ፡ ሶርያና ፡ ስለ ፡ ፊኒቅያ ፡ ስለ ፡ ትንሽ ፡ እስያም ።

፩ ፤ ስለ ፡ ሶርያ ፡ ትንሽ ፡ አሳስባችኋለሁ ። ይህም ፡ አገር ፡ ያለው ፡ በጰለስቲና ፡ ሰሜን ፡
ነው ። በሰሜን ፡ ወገን ፡ ከትንሽ ፡ እስያ ፡ በምሥራቅ ፡ ወገን ፡ ከኤፍራጥስ ፡ ወን
ዝና ፡ ከዐረብ ፤ በደቡብ ፡ ወገን ፡ ክፍልስጥኤምና ፡ ከዐረብ ፡ ክፍል ፤ በምዕራብ ፡
ወገን ፡ ከሜዲቴራኒያን ፡ ባሕር ፡ ይዋሰናል ።

፪ ፤ ስለ ፡ ሶርያ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ በመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ተነግሮዋል ። ከዳዊት ፡ ዘመን ፡ ጀምሮ ፡
ሮማውያን ፡ እስኪ ፡ ገዙበት ፡ እስከ ፡ ክርስቶስ ፡ ዘመን ፡ ድረስ ፡ ሕዝቡ ፡ ከአይሁድ
ጋር ፡ ዘወትር ፡ ሲዋጉ ፡ ይኖሩ ፡ ነበር ።

፫ ፤ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ከተማቸው ፡ አንጾኪያ ፡ ይባል ፡ ነበር ። ይህም ፡ በዓለም ፡ የታ
ወቀ ፡ ከተማ ፡ ነበር ። ይህም ፡ የቅዱስ ፡ ሉቃስ ፡ አገር ፡ ነው ። በዚሁ ፡ አገር ፡
አንድ ፡ ጊዜ ፡ ቅዱስ ፡ ጴጥሮስና ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ተቀምጠውበት ፡
ነበር ። የክርስቶስ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርት ፡ መጀመሪያ ፡ ክርስቲያን ፡ ተብለው ፡ የተጠ
ሩበት ፡ በዚሁ ፡ ስፍራ ፡ ነው ።

፬ ፤ ደግሞ ፡ ደማስቆ ፡ የተባለው ፡ ሌላው ፡ የሶርያ ፡ ከተማ ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ መቶ ፡
ሠላሳ ፡ ስድስት ፡ ማይል ፡ የራቀ ፡ ከአብርሃም ፡ ዘመን ፡ ጀምሮ ፡ የታወቀ ፡ ነው ።
ይህም ፡ ደግሞ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ በመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ተነግሮዋል ። በዚህም ፡ ስፍራ ፡
ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ በተኣምራት ፡ የክርስቲያንን ፡ ሃይማኖት ፡ ተቀብሎዋል ።

፭ ፤ በዚህ ፡ ከተማ ፡ በቀድሞ ፡ ዘመን ፡ ይሠራ ፡ የነበረው ፡ ሰይፍና ፡ ጐራዴ ፡ ሌላም ፡
የሚቈርጥ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ እጅግ ፡ ስመ ፡ ጥሩ ፡ ነበር ። ሕዝቡ ፡ ቀድሞ ፡ ይህን ፡
ሲሠሩበት ፡ የነበራቸው ፡ ብልሀት ፡ ዛሬ ፡ ጠፍቶባቸዋል ። በዚኸው ፡ ከተማ ፡
የሚኖሩት ፡ ባላገሮች ፡ እጅግ ፡ የሚያምር ፡ ሐር ፡ በመሥራታቸው ፡ በጣም ፡ የታ
ወቁ ፡ ናቸው ። የሚሠሩት ፡ ዕቃ ፡ ጥራቱ ፡ እጅግ ፡ የተመሰከረለት ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡
በየትም ፡ የደማስቆ ፡ ሥራ ፡ ይባላል ።

፮ ፤ ደግሞ ፡ በሶርያ ፡ አንዱ ፡ በቅዱስ ፡ መጽሐፍ ፡ የተነገረው ፡ ታድሞር ፡ ይባላል ፤
ይህንም ፡ ለንግድ ፡ ይመቻል ፡ ብሎ ፡ የሠራው ፡ ሰሎሞን ፡ ነው ። ስፋቱ ፡ ዐሥር ፡
ማይል ፡ ይሆናል ። ዛሬ ፡ ግን ፡ ፍራሹ ፡ ብቻ ፡ ይታያል ። በዚህም ፡ ስፍራ ፡
የሚታየው ፡ የቀድሞው ፡ ፍራሽ ፤ የተጠረበው ፡ ድንጋይ ፡ ምሰሶው ፤ ሌላም ፡
ልዩ ፡ ልዩ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ሲታይ ፡ ያ ፡ ስፍራ ፡ እጅግ ፡ ታላቅ ፡ ከተማ ፡ እንደ ፡
ነበረ ፡ ይታወቃል ። ዛሬ ፡ ግን ፡ ያን ፡ ስፍራ ፡ ፓልሚራ ፡ ይሉታል ።

፯ ፤ ከደማስቆስ ፡ ፴፯ ፡ ማይል ፡ ራቅ ፡ ብሎ ፡ በሰሜን ፡ ምዕራብ ፡ ወገን ፡ የባልቤክ ፡
ከተማ ፡ ፍራሽ ፡ ይገኛል ። ይህ ፡ ከተማ ፡ በሖቆርያት ፡ ዘመን ፡ በጣም ፡ የታወቀ ፡

ስፍራ ፡ ነበር ፤ ስሙን ፡ ሔሊዎፖሊስ ፡ ወይም ፡ የፀሓይ ፡ ከተማ ፡ ይሉታል ። አሁን ፡ ግን ፡ ፍራሹ ፡ ብቻ ፡ ይታያል ። ከአንድ ፡ ሺሕ ፡ የሚበዙ ፡ ባላገሮች ፡ ይኖሩበታል ።

፰፤ በሚዴቴራኒያን ፡ ባሕር ፤ ጠረፍ ፡ ስላለው ፡ ፊኒቂያ ፡ ስለ ፡ ተባለው ፡ አውራጃ ፡ ለመናገር ፡ አልረሳሁም ። ይህም ፡ ስፍራ ፡ ጢሮስ ፡ ሲዶና ፤ ጵቶልሚስ ፤ ሌሎችም ፡ የታወቁ ፡ ስፍሮች ፡ ያሉበት ፡ አውራጃ ፡ ነው ። በቀድሞ ፡ ዘመን ፡ ፊኒቂያኖች ፡ በንግድና ፡ በባሕር ፡ መንገድ ፡ በሌላም ፡ ብልሀት ፤ ስመ ፡ ጥሩዎች ፡ ነበሩ ። ቀድሞ ፡ በገዛ ፡ ራሳቸው ፡ የሚኖሩ ፡ ሕዝብ ፡ ነበሩ ። በኋላ ፡ ግን ፡ አገራቸው ፡ የሶርያ ፡ ክፍል ፡ ሆነ ።

፱፤ እንደ ፡ ሌሎች ፡ አገሮችም ፡ ተረግጦ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ የመሆንና ፡ የመፍረስ ፡ መልክ ፡ ያሳያል ። ሶርያ ፡ እንደቀድሞው ፡ ያለ ፡ ስም ፡ የለውም ። ጰለስቲናም ፡ እንዲሁ ፡ ነው ።

፲፤ ትንሽ ፡ እስያ ፡ ወይም ፤ ዛሬ ፡ እንደሚጠራው ፡ ናቶሊያ ፡ ያለው ፡ ከሚዴቴራኒያን ፡ ባሕር ፡ በሰሜን ፡ ምሥራቅ ፡ ወገን ፡ ነው ። አገሩ ፡ ሞላላ ፡ ነው ። በሰሜን ፡ ወገን ፡ ከጥቊር ፡ ባሕር ፡ በምዕራብ ፡ ወገን ፡ ከኤጀን ፡ ባሕር ፡ በምሥራቅ ፡ ወገን ፡ ከሶርያና ፡ ከሞስጶታሚያ ፤ ከአርማኒያ ፡ ይዋሰናል ።

፲፩፤ ከምሥራቅ ፡ እስከ ፡ ምዕራብ ፡ ርዝመቱ ፡ ስድስት ፡ መቶ ፡ ማይልስ ፡ ይሆናል ። ስፋቱ ፡ አራት ፡ መቶ ፡ ማይል ፡ ነው ። ከሕዝቡ ፡ የሚበዙት ፡ እስላሞች ፡ ናቸው ። ዋናው ፡ ከተማቸው ፡ ስሚርና ፡ ይባላል ። ከዚህም ፡ መርከቦች ፡ እየተነሡ ፡ በለስና ፡ ተምር ፡ ሌላም ፡ ነገር ፡ ይዘው ፡ ይመጣሉ ።

፲፪፤ ትንሽ ፡ እስያ ፡ ከጥንት ፡ የቈየ ፡ አገር ፡ መሆኑ ፡ ይታያል ። በዚሁ ፡ አገር ፡ በልዩ ልዩ ፡ ጊዜ ፡ ብዙ ፡ መንግሥታት ፡ እየተነሡ ፡ ወደ ፡ ታላቅነት ፡ ደርሰውበታል ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ትልቅ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ አልሆነም ። ተክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ ፭፻ ፡ ዓመት ፡ የልድያ ፡ መንግሥት ፡ በትንሽ ፡ እስያ ፡ ነበር ። ፮፻፶፪ ፡ ዓመት ፡ ተክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ የነበረው ፡ ንጉሣቸው ፡ ግን ፡ አርዲስ ፡ ይባላል ።

፲፫፤ የልድያ ፡ የመጨረሻው ፡ ንጉሥ ፡ ክሩሲስ ፡ ይባላል ። ሀብታም ፡ በመሆኑ ፡ ስመ ፡ ጥሩ ፡ ነበር ። እስከ ፡ ዛሬ ፡ ሀብታም ፡ እንደ ፡ ክሩሲስ ፡ ይባላል ። እንዲህ ፡ ባለጸጋ ፡ ሳለ ፡ ፭፻፵፮ ፡ ተክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ ቂሮስ ፡ የፋርስ ፡ ንጉሥ ፡ ድል ፡ አደረገው ።

፲፬፤ ፫፻፴፬ ፡ ተክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ ታላቁ ፡ እስክንድር ፡ መጥቶ ፡ ድል ፡ እስኪያደርግ ፡ ድረስ ፡ ልድያ ፡ ከዚህ ፡ ወድያ ፡ ትንሽ ፡ እስያን ፡ ጨምሮ ፡ ለፋርስ ፡ መንግሥት ፡ ተገዛ ።

፲፭፤ ፫፻ ፡ ዓመት ፡ ተክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ የልድያ ፡ ክፍል ፡ የነበረው ፡ ጳንጦስ ፡ ነጻ ፡ ወጥቶ ፡ በራሱ ፡ አዳሪ ፡ ሆነና ፡ ብዙ ፡ ዓመት ፡ ገናና ፡ መንግሥት ፡ እንደሆነ ፡ ቈየ ። ማትሪዳስ ፡ ፮ኛ ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ ከሮማውያን ፡ ጋር ፡ ጦርነት ፡ አድርጎ ፡ ነበር ።

፲፮ ፤ በብልሀቱና ፡ በድፍረቱ ፡ የመንግሥቱን ፡ ጄኔራሎች ፡ አታለለ ፡ ፳፬ ፡ ተክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ ድል ፡ ሆነና ፡ መንግሥቱ ፡ ከትንሽ ፡ እስያ ፡ ጋር ፡ የሮም ፡ መንግሥት ፡ ግዛት ፡ እንዲሆን ፡ ግድ ፡ ሆነበት ።

፲፯ ፤ በትንሽ ፡ እስያ ፡ ጦርነት ፡ ሳይሆን ፡ በገሩ ፡ ሕዝብ ፡ መላበት ። በዙሪያውም ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ስፍራ ፡ ያሉት ፡ ከተሞች ፡ ተነሡ ። በልድያ ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፡ ኤፌሶን ፡ የታወቀ ፡ ከተማ ፡ ነበር ። የሚታይም ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ነበረበት ፡ በዓለም ፡ ከተደረጉት ፡ ከሰባቱ ፡ ተአምራት ፡ አንዱ ፡ እርሱ ፡ ነው ፡ ይባላል ።

፲፰ ፤ የዚሁ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ሥራ ፡ የተጨረሰው ፡ በመቶ ፡ ኻያ ፡ ዓመት ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ ኤሮስትራቱስ ፡ የተባለ ፡ ሰው ፡ ለመታሰቢያው ፡ ብሎ ፡ ፈጽሞ ፡ ከምድር ፡ እስኪጠፋ ፡ ድረስ ፡ በእሳት ፡ አቃጠለው ።

፲፱ ፤ ደግሞ ፡ በትንሽ ፡ እስያ ፡ ሌሎች ፡ አያሎች ፡ ያማሩ ፡ ከተሞች ፡ ነበሩ ። ከነዚህም ፡ አያሎችን ፡ ሐዲስ ፤ ኪዳን ፡ ያመለክተናል ። አንዱ ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ የተወለደበት ፡ አገር ፡ ጠርሴስ ፡ ነው ። ደግሞ ፡ ጴርጋሞስ ፡ ቲያቲራ ፡ ሳርዲስ ፡ ፊላዲልፊያ ፡ ላዖቅያ ፤ እነዚህ ፡ ሁሉ ፡ በራእየ ፡ ዮሐንስ ፡ መጽሐፍ ፡ ተነግረዋል ።

፳ ፤ መጀመርያ ፡ ክርስትና ፡ የተመሠረተው ፡ ጳውሎስ ፤ በርናባስ ፤ ሲላስ ፡ ጢሞቴዎስ ፤ ሉቃስ ፤ ምናልባት ፡ ሌሎችም ፤ እነዚህ ፡ ሁሉ ፡ በሠሩበት ፡ በትንሽ ፡ እስያ ፡ ክፍል ፡ ነው ።

## ጥያቄ ።

፩ ፤ ሶርያ ፤ ያለው ፡ በወዴት ፡ ነው ፡ ? ከማን ፡ ይዋሰናል ፡ ?
፪ ፤ የሶርያ ፡ ሕዝብ ፡ እንደምን ፡ ያሉ ፡ ናቸው ፡ ?
፫ ፤ የሶርያ ፡ ዋና ፡ ከተማ ፡ ማን ፡ ይባላል ፡ ?
በአንጾኪያ ፡ አንድ ፡ ትልቅ ፡ የሆነው ፡ ነገር ፡ ምንድርነው ፡ ?
፬ ፤ በደማስቆስ ፡ ምን ፡ ተደረገ ፡ ? በዚያ ፡ ስፍራ ፡ የተደረገው ፡ ምንድርነው ፡ ?
፭ ፤ ደማስቆስ ፡ በቀድሞ ፡ ዘመን ፡ መታወቁ ፡ በምንድርነው ፡ ?
፮ ፤ ታድሙር ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ?
፯ ፤ የባልቤክ ፡ ፍራሽ ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ?
፰ ፤ ፊኒቅያ ፡ እንደምን ፡ ሆነ ፡ ?
ምን ፡ አለበት ፡ ምን ፡ ይገኝበታል ፡ ?
ፊኒቅያዎች ፡ እንደምን ፡ ሆኑ ፡ ?
፱ ፤ ሶርያ ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ? ዛሬ ፡ ስሙ ፡ ማን ፡ ይባላል ፡ ?
፲ ፤ ትንሽ ፡ እስያ ፡ ያለበትና ፡ ዳርቻው ፡ እስከ ፡ የት ፡ ድረስ ፡ ነው ፡ ?
፲፩ ፤ ስፋቱ ፡ አገዛዙና ፡ ሕዝቡ ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ?
ስሚርና ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ?
፲፪ ፤ ትንሽ ፡ እስያ ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ?

ልድያ ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ? ኤርዲስ ፡ ?
፲፫ ፡ ስለ ፡ ክሪሱስ ፡ ምን ፡ ትላለህ ፡ ?
ድል ፡ ያደረገው ፡ ማነው ፡ ?
፲፬ ፡ ጳንጦስ ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ?
ሚቲሪዳስ ፡ ፮ኛ ፡ ምን ፡ አደረገ ፡ ?
፲፭ ፡ ሚቲሪዳስን ፡ ድል ፡ ያደረገው ፡ ማነው ፡ ?
፲፮ ፡ ኤፌሶን ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ?
፲፯ ፡ የዲያና ፡ ቤተ ፡ ጣዖት ፡ ፍጻሜው እንዴት ፡ ሆነ ፡ ?
በምን ፡ ጠፋ ፡ ?
፲፰ ፡ በትንሽ ፡ እስያ ፡ የነበሩ ፡ ሌሎች ፡ ከተሞች እንዴት ፡ ሆኑ ፡ ?
፳ ፡ በትንሽ ፡ እስያ ፡ ክርስትናን ፡ የመሠረተ ፡ ማነው ፡ ?

## ምዕራፍ ፡ ፴፮ ፡ እስያ ።

### ስለ ፡ እያሎች ፡ ነገድ ፡ ትንሽ ፡ የሚታይ ።

፩ ፡ ከእስያ ፡ በጣም ፡ የታወቁትን ፡ አገሮች ፡ ታሪክ ፡ ተርኬላችኋለሁ ። ደግሞ ፡ ከነ ዚሁ ፡ አያሎች ፡ ግዛቶች ፡ እያንዳንዱ ፡ ሰፊ ፡ አውራጃ ፡ ነው ። የነዚህን ፡ ታሪክ ፡ አብዝኅኙን ፡ በዚች ፡ መጽሐፍ ፡ ልነግራችሁ ፡ እችላለሁ ።

፪ ፡ የእስያን ፡ ሰሜን ፡ ክፍል ፡ መጀመሪያ ፡ የቈረቈሩ ፡ ሲቲያኖች ፡ የተባሉት ፡ ሕዝብ ፡ ጦረኞችና ፡ እንደ ፡ አራዊት ፡ ያሉ ፡ ናቸው ። በቀስትና ፡ በፍላፃ ፡ የሚወዳደራ ቸው ፡ የለም ። አያሌዎች ፡ የእስያና ፡ የአውሮጳ ፡ ነገሥታት ፡ ይገዙልናል ፡ ሲሉ ፡ ፈትነው ፡ ነበር ። ዳሩ ፡ ግን ፡ አልሆነላቸውም ፡ ብዙ ፡ ጊዜም ፡ ድል ፡ መቱዋቸው ።

፫ ፡ በሠለጠኑት ፡ አገሮች ፡ በደቡብ ፡ በኩል ፡ ኍልቍ ፡ መሳርት ፡ የሌላቸው ፡ ሲቲያኖች ፡ ተጥለቀለቁባቸው ። ከሲቲያኖች ፡ አንዱ ፡ ነገድ ፡ እጅግ ፡ ኀይለኛ ፡ የሆነውን ፡ የአፓርቲያን ፡ መንግሥት ፡ መሠረተ ።
ይኸውም ፡ መንንግሥት ፡ በኋላ ፡ ግዛቱን ፡ በፋርስና ፡ በሌሎች ፡ አገሮች ፡ ያስ ፋፋ ፡ ነው ። ይህ ፡ መንግሥት ፡ ተክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ ከ፪፻፶ ፡ ዓመት ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ፩፻ ፡ ዓመት ፡ ገዝቶአል ።

፬ ፡ በኋለኞትም ፡ ዘመናት ፡ አውራጃውን ፡ ታርታሪ ፡ የተባሉት ፡ እነዚያው ፡ ሲቲ ያኖች ፡ ይኖሩበታል ። ሕዝቡ ፡ ከቀድሞዋቸው ፡ አብልጠው ፡ እጅግ ፡ አልሠለ ጡም ። ከታርታሮች ፡ መካከል ፡ በየጊዜው ፡ አያሎች ፡ አሸናፊች ፡ ተነሥተዋል ።

፭ ፡ በጥንት ፡ ዘመን ፡ ህንድ ፡ ዛሬ ፡ የምሥራቅ ፡ ህንዶች ፡ የምንላቸው ፡ በም ዕራብ ፡ ወገን ፡ ለሚኖሩት ፡ ሕዝብ ፡ የታወቁት ፡ በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ነው ። አገራ ቸውን ፡ ሲሚራሚስ ፡ የተባለች ፡ ንግሥት ፡ ወረረችው ። ደግሞ ፡ ታላቁ ፡ እስ

ከንድርና ፡ ሌሎችም ፡ አሸናፎች ፡ እንዲሁ ፡ አድርገዋል ። ዛሬ ፡ ያሉት ፡ ሀን ዶች ፡ እጅግ ፡ የሚያስደንቁ ፡ ናቸው ። ለጣያትም ፡ ይሰግዳሉ ።

፯ ፡ ህንድ ፡ በውስጡ ፡ ሂንዱስታንና ፡ በምሥራቅ ፡ ወገንም ፡ ሌሎች ፡ ሰፋፊ ፡ አውራጃዎች ፡ አሉት ። ከዓለም ፡ ይህንን ፡ ክፍል ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ የሚያህል ፡ የእንግሊዝ ፡ ኀይል ፡ ደፍጥቶታል ። ከባላገሮቹ ፡ ወገን ፡ ገዦች ፡ የነበሩትን ፡ እየወጉ ፡ አስገበሩዋቸው ።

፰ ፡ ቱርኮች ፡ ወይም ፡ ኦቶማንሶች ፡ የተባሉ ፡ ሕዝብ ፡ ጥንት ፡ መሠረታቸው ፡ በእስያ ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ በኤውሮጳ ፡ ክፍል ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ ስለ ፡ ኖሩ ፡ ስለ ነርሱ ፡ መተረክና ፡ መናገር ፡ የተመቸና ፡ የተገባ ፡ ነው ።

፱ ፡ ጃፓን ፡ ፴፫ ፡ ሚሊዮን ፡ ባላገሮች ፡ ያሉበት ፡ ሰፊ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ አገር ፡ ነው ። ጃፓኖች ፡ በቺን ፡ ምሥራቅ ፡ በብዙ ፡ ደሴቶች ፡ ላይ ፡ ይኖራሉ ። ከነዚህም ፡ ሰፊው ፡ ደሴት ፡ ኒፎን ፡ ይባላል ። ሕዝቡ ፡ ባንድ ፡ ሰፊ ፡ ከተማ ፡ ውስጥ ፡ እየተጋፉ ፡ ታፍገው ፡ ይኖራሉ ። በሃይማኖታቸው ፤ በጠባያቸውና ፡ በልማዳቸው ፡ ሁሉ ፡ ፍጹም ፡ ቺኖችን ፡ ይመስላሉ ።

፲ ፡ ጃፓን ፡ መሬቱ ፡ ፍሬያማና ፡ ለም ፡ ነው ። ትንባሆ ፤ ሻይ ፤ ድንች ፤ ሩዝ ፡ ስንዴም ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ ይዘራበታል ። ጃፓኖች ፡ ዋና ፡ ሥራቸው ፡ ግብርና ነው ። ደግሞ ፡ ዋና ፡ የእጅ ፡ ሥራቸው ፡ ሐርና ፡ ጥጥ ፡ ስኒ ፡ ነው ። እንዲያ ውም ፡ ተቺን ፡ ሥራ ፡ የበለጠ፡ነው ፡ ይባላል ። ሥዕልና ፡ ደንጊያ ፡ መጥረብ ፡ ሌላም ፡ ሁሉ ፡ ለመሥራት ፡ ይችላሉ ። የተፈጥሮ ፡ ዕውቀት ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ጠባይ ፡ ቁም ፡ ነገረኝነትና ፡ መስማማት አላቸው ።

፲፩ ፡ ታሪካቸው ፡ እጅግ ፡ ትንሽ ፡ የሆነ ፡ የሚያስደንቁ ፡ ሌሎች ፡ አያሎች ፡ መን ግሥታት ፡ በእስያ ፡ አሉ ። ከነዚህም ፡ ሲያም ፡ ከቺን ፤ ቺን ፡ ቡርማን ፡ የን ጉሠ ፡ ነገሥት፡መንግሥት ፤ ካቡር ፤ ቤሉቺስታን ፤ ሌሎችም ፡ ናቸው ። ከነዚህ ፡ በቀር ፡ ሌሎች ፡ በእስያ ፡ ሰሜን ፡ ወገን ፡ የሚኖሩ ፡ ታርታር ፡ የተባሉ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ነገዶች ፡ አሉ ። ከብዙ ፡ ዘመን ፡ ጀምረው ፡ ታሪካቸውን ፡ ለኋላ ፡ ሰዎች ፡ ሳይተዉ ልን ፡ በነዚህ ፡ አውራጃዎች ፡ ሲዞሩ ፡ የኖሩ ፡ ወገኖች ፡ ናቸው ። በዚህ ፡ በሰፊ ፡ አገር ፡ ላይ ፡ የሚገዛ ፡ የመስኮብ ፡ የረሺያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ነው ።

## ጥ ያ ቄ ።

፩ ፤ ሲቲያኖች ፡ እንዴት ፡ ያሉ ፡ ሕዝብ ፡ ኑረዋል ፡ ?
፪ ፤ ፓርቲያ ፡ ምንድርነው ።
፫ ፤ ጥንት ፡ ሲቲያኖችና ፡ ፓርቲያኖች ፡ ይዘውት ፡ የነበረው ፡ አገር ፡ ማን ፡ ተባለ ።
ታርታሮች ፡ እንደ፡ቀድሞቹ፡ሲቲያኖችና ፡ ፓርቲያኖች ፡ሆነው ፡ ኖሩን ፡ ?
፬ ፤ ህንድ ፡ ወይም ፡ ሂንዱስታን ፡ እንደምን ፡ ሆነ ፡ ? ወሰኑ ፡ (እስከ ፡ የት፡ነው ፡ )

እንደምን ፡ ተወሰኗል ።
ከቺን ፡ በወዴት ፡ በኩል ፡ ነው ፡ ?
ከፋርስ ፡ ወዴት ፡ ነው ፡ ?
ከፐለስታይን ፡ ወዴት ፡ ነው ፡ ?
፮ ፤ በሂንዱስታን ፡ ያለው ፡ እንግሊዝ ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ?
፯ ፡ ቱርኮች ፡ ወይም ፡ ኦቶማኖች ፡ እንዴት ፡ ሆኑ ፡ ?
፰ ፤ ጃፓን ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ?
፱ ፤ የጃፓኖች ፡ የእጅ ፡ ሥራ ፡ ምንድነው ፡ ?
፲ ፤ ታሪካቸው ፡ በጣም ፡ ያልታወቀው ፡ በዚያ ፡ የሚኖሩ ፡ ሕዝብ ፡ ምን
ድን ፡ ናቸው ፡ ?
የሰሜን ፡ እስያ ፡ ሕዝብ ፡ ክፍል ፡ ማን ፡ ይባላሉ ፡ ?

## ምዕራፍ ፡ ፴፯ ፡ እስያ ።

### የእስያን ፡ ታሪክ ፡ መመርመር ።

፩ ፤ እንደ ፡ ገና ፡ ወደ ፡ ኋላችን ፡ ተመልሰን ፡ የእስያን ፡ ታሪክ ፡ እንመርምር ። በዚህ ፡ የዓለም ፡ አራተኛ ፡ ክፍል ፡ በሚሆን ፡ በእስያ ፡ እጅግ ፡ የሚያስደንቅ ፡ የሆነ ፡ የሰው ፡ ታሪክ ፡ ተደርጓል ። በዚህ ፡ አዳምና ፡ ሔዋን ፡ ተፈጠሩ ። ከጥፋት ፡ ውሃ ፡ በፊት ፡ የነበሩ ፡ ሕዝብ ፡ ሁሉ ፡ በኤፍራጥስ ፡ ወንዝ ፡ ዳር ፡ ይኖሩ ፡ ነበር ።

፪ ፤ የኖኅ ፡ መርከብ ፡ የቆመበት ፡ ስፍራ ፡ በእስያ ፡ ነው ። ደግሞ ፡ ሕዝቡ ፡ ከተሞች ፡ መሥራትና ፡ ሕዝብ ፡ መሆን ፡ የጀመሩበት ፡ በዚሁ ፡ ላይ ፡ ነው ። ከዚህ ፡ ስፍራ ፡ መጀመሪያ ፡ ታላቅ ፡ መንግሥት ፡ ተነሣ ። አይሁድ ፡ ሕዝብ ፡ መሆን ፡ የጀመሩት ፡ በዚህ ፡ ነው ። በብሉይ ፡ ኪዳን ፡ የተነገረው ፡ የሆነው ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ በዚህ ፡ ስፍራ ፡ ነው ።

፫ ፤ ከዘለዓለም ፡ የነበረ ፡ እውነተኛ ፡ ሕያው ፡ አምላክ ፡ እንዳለ ፡ ሃይማኖት ፡ ያስተማረን ፡ በእስያ ነው ። የርሱን ፡ ሃይማኖት ፡ ለመመሥረት ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ የተገለጠውና ፡ የራእይንም ፡ ዕውነት ፡ በደሙ ፡ ያተመው ፡ በዚሁ ስፍራ ፡ ነው ።

፬ ፡ ሙሐመድ ፡ ተነሥቶ ፡ ሃይማኖቱን ፡ የመሠረተበት ፡ በእስያ ፡ ነው ። በዓለም ፡ ካሉት ፡ ሕዝብ ፡ የሚበዙት ፡ ሃይማኖቱን ፡ ተቀብለውታል ። ብዞዎቹም ፡ ሌሎች ፡ ሃይማኖቶች ፡ የተጀመሩ ፡ በእስያ ፡ ነው ።

፭ ፡ አያሌዎች ፡ ታላላቆች ፡ መንግሥታት ፡ በእስያ ፡ ኖረዋል ። ምክንያታቸውንም ፡ ታሪክ ፡ ይሰጠናል ። ፊት ፡ እንደ ፡ ተናገርሁት ፡ መጀመርያ ፡ ታሪክ ፡ ያለው ፡ የአሶር ፡ መንግሥት ፡ ነው ። ወዲያው ፡ የፋርስ ፡ መንግሥት ፡ ይከተለዋል ፤ ይህም ፡ በዙሪያው ፡ ያሉትን ፡ አገሮች ፡ ሁሉ ፡ የሚውጣቸው ፡ ይመስላል ፤ እጅግ ፡

የሰው ፡ ብዛት ፡ ያለው ፡ በዓለም ፡ የታወቀ ፡ መንግሥት ፡ ቺን ፡ ነው ። እርሱም ፡ ከሌላ ፡ ይልቅ ፡ የጸና ፡ ነው ።

፮ ፤ በብዙ ፡ አገሮች ፡ ላይ ፡ መንግሥታቸውን ፡ አስፋፍተው ፡ ይኖሩ ፡ የነበሩት ፡ ሳራሲን ፡ የተባሉት ፡ ሕዝብ ፡ ጥንት ፡ የተነሡት ፡ ከእስያ ፡ ነው ። ጳለስቲናን ፡ ሞሶጶታሚያን ፡ ሶርያን ፡ ትንሽ ፡ እስያን ፡ ከኤውሮጳና ፡ ከአፍሪካም ፡ ክፍል ፡ ጨምረው ፡ እነዚህን ፡ ሁሉ ፡ አገሮች ፡ ይገዙዋቸው ፡ የነበሩ ፡ ቱርኮች ፡ የተነሡት ፡ ከእስያ ፡ ነው ።

፯ ፤ ከሌላው ፡ ዓለም ፡ ይልቅ ፡ ምናልባት ፡ እጅግ ፡ የበለጠ ፡ ታሪክ ፡ ያለው ፡ ከእስያ ፡ አንድ ፡ ክፍል ፡ ይኖር ፡ ይሆናል ። ያም ፡ ስፍራ ፡ ይህ ፡ ነው ። ሜዲቴራኒያን ፡ በምዕራብ ፤ አርማኒያ ፡ በሰሜን ፡ ፋርስ ፡ በምሥራቅ ፤ ዐረብ ፡ በደቡብ ፡ ሆኖ ፡ በነዚህ ፡ መኻከል ፡ ያለው ፡ አገር ፡ ነው ። መጀመሪያ ፡ የሰው ፡ ዘር ፡ የተባዛበት ፡ በዚህ ፡ ስፍራ ፡ ነው ። በመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ የተነገረው ፡ ተአምራት ፡ ሁሉ ፡ የተደረገበት ፤ ነቢያት ፡ ሁሉ ፡ የነበሩበት ፡ በዚሁ ፡ ነው ። ኢየሱስ ፡ የኖረበት ፡ ያስተማረበትና ፡ የሞተበትም ፡ በዚሁ ፡ አገር ነው ።

፰ ፤ ደግሞም ፡ ከዓለም ፡ ሁሉ ፡ በፊት ፡ ሰው ፡ የነበረበት ፡ በእስያ ፡ ነው ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ሕዝቡ ፡ ምንም ፡ በመኻከላቸው ፡ ታምራት ፡ ቢደረግና ፡ እምላካዊ ፡ መምህር ፡ ቢገለጽ ፡ ከሃይማኖት ፡ ዕውቀትና ፡ ለኑሮ ፡ ምቾትና ፡ ደስታ ፡ ከሚሰጥ ፡ ዕውቀት ፡ ተለይተው ፡ ከኤውሮጳና ፡ ከአሜሪካ ሕዝብ ፡ እጅግ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ቀርተዋል ።

፱ ፤ በእስያ ፡ ክፍል ፡ ከሚኖሩት ፡ ሕዝብ ፡ ብዙዎቹ ፡ አምልኮ ፡ ባዕድ ፡ የሚወዱ ፡ ናቸው ። በቅንነት ፤ በገርነት ፡ እግዚአብሔርን ፡ የሚያመልኩ ፡ እጅግ ፡ ጥቂቶች ፡ ናቸው ። ፩፻ ፡ ሚልዮን ፡ ሕዝብ ፡ ባለበት ፡ መኻከል ፡ በእስያ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በጣም ፡ አልታወቀም ። ምንም ፡ ሀብታሞች ፡ ነገሥታትና ፡ መኳንንት ፡ ሁነው ፡ ባጌጠ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ቢኖሩ ፡ ምንም ፡ ወርቅና ፡ ዕንቍ ፡ ቢኖራቸው ፡ ሕዝቡ ፡ ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ እናኑዋራቸው ፡ በድንቍርና ፤ በድኅነትና ፡ በመዋረድ ፡ ነው ።

፲ ፤ በእስያ ፡ ታሪክ ፡ እንደሚታየው ፡ በአገሩ ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ ሁከትና ፡ መለዋወጥ ፡ ሲሆን ፡ የሕዝቡ ፡ ሁኔታ ፡ ከቶ ፡ አይለወጥም ። በኤውሮጳና ፡ በዩናይትድ ፡ እስቴትስ ፡ አሜሪካ ፡ ብርቱ ፡ መሻሻል ፡ ይደረጋል ። በየዓመቱ ፡ ለሕዝብ ፡ ጥቅም ፡ የሚሆን ፡ አዳዲስ ፡ ብልሀት ፡ ያወጣሉ ።

፲፩ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ በእስያ ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ የለም ። ማነኛውም ፡ ቢነግሥ ፡ ሕዝቡ ፡ እንደባሮች ፡ ናቸው ፤ ትምህርትም ፡ አይገኝበትም ፤ ነጻነት ፡ በዚያ ፡ አልታወቀም ። እውነተኛነትም ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ አይደለም ፤ በጎ ፡ ሥራም ፡ ዋጋ ፡ አያወጣም ። አገራችንን የሚያስወድደን ፡ ምቾት ፡ የምንለው ፡ በዚህ ፡ ሰፊ ፡ በሆነው ፡ አገር ፡ (በእስያ) አይገኝም ። እንዲያው ፡ እግዚአብሔር ፡ ዕድልና ፡ የተፈጥሮ ፡ ሀብት ፡ ሰጥቶታል ።

፲፪ ፤ በእስያ ፡ ዋናው ፡ ችግር ፡ የወንጌል ፡ ትምህርት ፡ ስለ ፡ ሌለ ፡ ብዙ ፡ አሰተኛ ፡ አምልኮ ፡

ገብቶባቸዋል ፡፡ ስልምና ፡ በእስያ ፡ እጅግ ፡ አድርጎ ፡ አሸንፋዋል ፡ በእንደዚህ ፡ ያለ ፡ አሰተኛ ፡ ሃይማኖት ፡ የሚያምን ፡ ዱስታና ፡ መልከም ፡ አገዛዝ ፡ እን ደማያገኝ ፡ የታወቀ ፡ ነው ፡፡

፲፫ ፡ ህንዶች ፡ በብራሕማን ፡ ያምናሉ ፡፡ ትልቅ ፡ አድርገው ፡ የሚያምኑትን ፡ አንዱን ፡ አምላካቸውን ፡ ብራሕማ ፡ ብለውታል ፡፡ ከርሱ ፡ በታች ፡ ያሉትን ፡ አነስተኞች ፡ አማልክት ፡ ዊሽኑ ፡ ሲዋ ፡ ይሉዋቸዋል ፡፡ ለነዚህም ፡ ልዩ ፡ ምስል ፡ ሠርተው ፡ ይሰ ግዳሉ ፡፡ ካህናቱን ፡ ብራሕማንስ ፡ ይሉዋቸዋል ፡፡

፲፬ ፡ ከዚህም ፡ በቀር ፡ ደግሞ ፡ የሚሰግዱለት ፡ ላማ ፡ የሚባል ፡ ጣዖት ፡ አላቸው ፡፡ ለዚሁም ፡ በታርታሬ ፡ ቤተ ፡ ጣዖት ፡ ሠርተውለታል ፡፡ ቺኖች ፡ በቡዳ ፡ ያምናሉ ፡ ሌሎችም ፡ ተከፍለው ፡ በሌሎች ፡ ጣዖታት ፡ ይታመናሉ ፡፡

፲፭ ፡ ስለዚህ ፡ እስያ ፡ በመላው ፡ ስለ ፡ ሰው ፡ መጨረሻና ፡ ስለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጠባይ ፡ በጨለማ ፡ የተሸፈነ ፡ አገር ፡ ነውና ፡ ድንቍርናና ፡ ስሕተት ፡ ባለበት ፡ አገር ፡ ሁሉ ፡ የሰው ፡ ጠባይ ፡ እንደዚህ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እናያለን ፡፡

## ጥ ያ ቄ ፡፡

፩-፪-፫-፬ ፡ አንድ ፡ የታወቀ ፡ ነገር ፡ በእስያ ፡ የተደረገው ፡ ምንድር ፡ ነው ፡ ?

፭ ፡ አስቀድሞ ፡ በታሪክ ፡ የተነገረለት ፡ መንግሥት ፡ የትኛው ፡ ነው ፡ ?
የፋርሶች ፡ መንግሥት ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ?
የቺን ፡ መንግሥትስ ፡ ?

፮ ፡ ሳራሴኖች ፡ እንዴት ፡ ሆኑ ፡ ? ቱርኮችስ ፡ ?

፯ ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ እጅግ ፡ ድንቅ ፡ ነገር ፡ የተደረገበት ፡ ከእስያ ፡ ክፍል ፡ የትኛው ፡ ነው ፡ ?

፰ ፡ ስለምን ፡ ይህ ፡ በተለይ ፡ በእስያ ፡ ተደረገ ፡ ?
የእስያ ፡ ሕዝብ ፡ ከኤውሮጳና ፡ ከአሜሪካ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ያሉበት ፡ በምን ፡ ምክንያት ፡ ነው ፡ ?

፱ ፡ የእስያ ፡ ሕዝብ ፡ (ሕይወት)ንብረት ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ?

፲ ፡ በእስያ ፡ ታሪክ ፡ የታወቀ ፡ ነገር ፡ ምንድር ፡ ነው ፡ ?
ስለዚህ ፡ አገርና ፡ ስለ ፡ ኤውሮጳ ፡ ምን ፡ ይነገራል ፡ ?

፲፩ ፡ እስያ ፡ ከኤውሮጳና ፡ ከአሜሪካ ፡ የሚለይበት ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ?

፲፪ ፡ ባገሩ ፡ የታወቀ ፡ ነገር ፡ ምንድር ፡ ነው ፡ ? የእስያ ፡ እኳኋን ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ? በዚያ ፡ እስልምና ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ?

፲፫ ፡ ሂንዱስታኖች ፡ ሃይማኖታቸውና ፡ እምነታቸው ፡ በምን ፡ ነው ፡ ?
ብራሕማን ፡ ምን ፡ ያስተምራል ፡ ?
ብራሕማን ፡ ማለት ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ?

፲፪ ፤ የታላቁ ፡ ጣዖት ፡ የላማ ፡ መቅደስ ፡ ወዴት ፡ ነው ፡ ?
ቺኖች ፡ የሚያመልኩ ፡ ፀምንድር ፡ ነው ፡ ?
ሌሎች ፡ ሕዝብ ፡ በምን ፡ ይታመናሉ ፡ ?
፲፫ መላው ፡ እስያ ፡ የተሳሳቱት ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ?
ዕለ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ አካሄድና ፡ ጠባይ ፡ ምን ፡ እናያለን ፡ ?

## ምዕራፍ ፡ ፴፰ ፡ አፍሪካ ።

### ስለ ፡ አፍሪካ ፡ ጂዎግራፊና ፡ ሕዝብ ።

፩ ፤ ከስድስቱ ፡ ዓለማት ፡ አንዱ ፡ አፍሪካ ፡ ነው ። አፍሪካ ፡ ሰፊ ፡ ነው ። የዓለምም ፡ አራተኛ ፡ ክፍል ፡ ይሆናል ። ከኤውሮጳ ፡ የሚለየው ፡ በሜዴቴራኒያን ፡ ባሕር ፡ ነው ። ከአሜሪካም ፡ በአትላንቲክ ፡ ውቅያኖስ ፡ ይለያል ። ከኙዮርክም ፡ ቢሆን ፤ ወይም ፡ ከቦስቶን ፡ ከአሜሪካ ፡ የሚቀርበው ፡ ክፍል ፡ ሦስት ፡ ሺሕ ፡ ማይል ፡ ይሆናል ። ነገር ፡ ግን ፡ በጊብሮልታር ፡ በኩል ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለኤውሮጳ ፡ በጣም ፡ ቅርብ ፡ ነው ።

፪ ፤ ከእስያ ፡ በኤርትራ ፡ ባሕር ፡ ይለያያል ። የሆነ ፡ ሆኖ ፡ እስያ ፡ ባንድ ፡ ወገን ፡ ሱዝ ፡ ካናል ፡ በሚባለው ፡ በኩል ፡ ከአፍሪካ ፡ ጋር ፡ ተጋጥሞአል ። ሙሴ ፡ ሌስፕስ ፡ መርከብ ፡ እንዲተላለፍ ፡ ብሎ ፡ አስቆፍሮ ፡ ያስከፈተው ፡ በዚህ ፡ በኩል ፡ ነው ።

፫ ፤ አፍሪካ ፡ ከሌላው ፡ ዓለም ፡ ይልቅ ፡ የታወቀው ፡ በጣም ፡ ትንሽ ፡ ነው ። ኤውሮጳች ፡ ደኅና ፡ አድርገው ፡ አፍሪካን ፡ አልመረመሩትም ። ከሕዝቡ ፡ የሚበልጡት ፡ ሻንቅሎች ፡ ናቸው ። ከነዚህም ፡ ብዝዎቹ ። በነገድ ፡ የተለያዩ ፡ ናቸው ። የሚበዙትም ፡ አራዊት ፡ ሕዝብ ፡ ናቸው ።

፬ ፤ ዓየሩ ፡ ሙቀት ፡ ያለው ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ለመጠጊያቸው ፡ የሚፈልጉት ፡ ትንሽ ፡ ጐጆና ፡ ትንሽ ፡ ልብስ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ቤታቸው ፡ የተዋረደ ፡ ነው ። ቅጠላቅጠሉን ፡ ጐጆ ፡ ሠርተው ፡ በትንሽ ፡ ቤት ፡ ይኖራሉ ። መቸውንም ፡ ልብሳቸው ፡ አንዲት ፡ ቍራጭ ፡ ጨርቅ ፡ ናት ፤ በወገባቸውም ፡ ይጠመጥሚታል ።

፭ ፤ ከሻንቅሎቹ ፡ በቀር ፡ ደግሞ ፡ ሌሎች ፡ አያሎች ፡ የአፍሪካ ፡ ዘሮች ፡ አሉ። ከጕበዕ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ሐበሻ ፡ ድረስ ፡ ያሉት ፡ ባላገሮች ፡ የጥንት ፡ ግብፃውያንነታቸውን ፡ ሳይለቁ ፡ ከቱርኮችና ፡ ከዐረቦች ፡ ከሌሎችም ፡ የተቀላቀሉ ፡ ናቸው። ቅድም ፡ አራዊት ፡ ሕዝብ ፡ ያልናቸው ፡ የጥንት ፡ የካርታጎች ፡ ዘሮች ፡ ናቸው። አገሩን ፡ አሸንፈው ፡ ከያዙት ፡ ከሳራሴኖችና ፡ ከቱርክ ፡ ከሌሎችም ፡ ጋር ፡ ተቀላቅለው ፡ ቀርተዋል ።

፮ ፤ ሰሐራ ፡ የሚባለውን ፡ ልክ ፡ የሌለውን ፡ በረሃና ፡ በዙሪያው ፡ ያለውን ፡ አውራጃ ፡ ሁሉ ፡ ጨምረው ፡ ፈረሶቻቸውንና ፡ ግመሎቻቸውን ፡ ይዘው ፡ ለማሰማ

ራት ፡ ወይም ፡ ለመዝረፍ ፡ ከአንዱ ፡ ወዳንዱ ፡ የሚዞሩ ፡ ዐረቦች ፡ ይዘውታል ።

፯ ፤ አፍሪካ ፡ በመላው ፡ ወደ ፡ ሥልጣኔ ፡ ያልደረሰ ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ ይታሰባል ፤ ከሕዝቡ ፡ የሚበዙት ፡ እስላሞች ፡ ናቸው ። ከነዚኽም ፡ እኩሌቶቹ ፡ አራዊት ፡ ሕዝብ ፡ የቀሩትም ፡ አሕዛቦች ፡ ናቸው ።

፰ ፤ በመኻከለኛው ፡ አፍሪካ ፡ አንበሳ ፤ ዝሆን ፤ አውራሪስ ፤ የሜዳ ፡ አህያ ፤ ሌሎችም ፡ አራዊት ፡ ይገኙበታል ። በደኑ ፡ ሁሉ ፡ ጦጣና ፡ ዝንጀሮ ፡ ይንጫጩበታል ። በጫካው ፡ ውስጥ ፡ ዘንዶና ፡ ሰጐን ፡ ሞልተዋል ። በሜዳው ፡ አጋዘንና ፡ ድኩላ ፡ የሜዳ ፡ ፍየል ፡ ተሰማርተው ፡ ይታያሉ ። በየወንዙና ፡ በየባሕሩ ፡ ጉማሬ ፡ ይታያል ። አዞ ፡ በረጋ ፡ ውሃ ፡ ውስጥ ፡ ትኖራለች ። አዕዋፍም ፡ በየስፍራው ፡ ሁሉ ፡ ይታያሉ ።

## ጥ ያ ቄ ።

በሰሜን ፡ በኩል ፡ አፍሪካ ፡ ከማን ፡ ይዋሰናል ፡ ? በምሥራቅስ ፡ ? በምዕራብስ ፡ ?
ልክ ፡ በደቡብ ፡ አኳያ ፡ ያለው ፡ ክፍል ፡ ማን ፡ ይባላል ፡ ?
በምሥራቅ ፡ አኳያ ፡ ያለው ፡ ማን ፡ ይባላል ፡ ?
በምዕራብስ ፡ ? በሰሜንስ ፡ አኳያ ፡ ያለው ፡ ?
ግብፅ ፡ ያለው ፡ በየትኛው ፡ ክፍል ፡ ነው ፡ ?
የሰሐራ ፡ በረሃ ፡ በወዴት ፡ ወገን ፡ ነው ፡ ?
ነጭ ፡ ዐባይ ፡ የሚፈሰው ፡ ወዴት ፡ ነው ፡ ?
እየጐረፈ ፡ ፈሳሹ ፡ ወዴት ፡ ይገባል ፡ ?
፩ ፤ አፍሪካ ፡ ከኤውሮጳና ፡ ከአሜሪካ ፡ በምን ፡ ይለያያል ፡ ?
ከኙዮርክ ፡ ወይም ፡ ከቦስቶን ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ይርቃል ፡ ?
፪ ፤ ከእስያ ፡ በምን ፡ ይለያያል ፡ ?
ከእስያ ፡ ጋር ፡ እንደ ፡ አንገት ፡ ሆኖ ፡ ያያያዘው ፡ የብስ ፡ ማን ፡ ይባላል ፡ ?
፫ ፤ አፍሪካ ፡ የታወቀ ፡ ነውን ፡ ?
ባላገሮቹ ፡ እንዴት ፡ ያሉ ፡ ናቸው ፡ ?
፬ ፤ ዓየሩሳ ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ?
ቤታቸው ፤ ልብስ ፡ አለባበሳቸው ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ?
፭ ፤ ሻንቅሎች ፡ እንደምን ፡ ያሉ ናቸው ፡ ?
ሌሎቹ ፡ ዘሮች ፡ እንደምን ፡ ያሉ ፡ ናቸው ፡ ?
ሁኔታቸውን ፡ ለመግለጽ ፡ ትችላለህን ፡ ?
፮ ፤ አፍሪካ ፡ እንደምን ፡ ይታሰባል ፡ ?
የሕዝቡ ፡ ኑሮ ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ?
በመኻከል ፡ አፍሪካ ፡ እንዴት ፡ ያሉ ፡ አውሬዎች ፡ ይገኛሉ ፡

## ምዕራፍ ፡ ፴፱ ፡ አፍሪካ ።

### ስለ ጥንታውያን የግብጽ ባለሥልጣኖች ።

፩ ፤ መጀመሪያ ፡ የአፍሪካ ፡ ሕዝብ ፡ የኖኅ ፡ ልጅ ፡ የካም ፡ ዘሮች ፡ ናቸው ፤ ይህ አገር ፡ ሰናዖር ፡ ለሚሉት ፡ ቅርብ ፡ ስለ ፡ ነበር ፡ የባብል ፡ ግንብ ፡ ከተሠራ ፡ በኋላ ፡ ከዚህ ፡ ተነሥተው ፡ ወደ ፡ ግብፅ ፡ ወረዱ ። የግብፅ ፡ መንግሥት ፡ ዋና ፡ ጥንታዊ ፡ ነው ፤ የመሠረተውም ፡ ከካም ፡ ልጆች ፡ አንዱ ፡ ሜኒስ ፡ የተባለው ፡ ነው ። ይህም ፡ የሆነው ፡ ፫፭፻፲፰ ፡ ተክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ ነው ፤ ወቅዱስ ፡ መጽሐፍ ፡ ሚስራይም ፡ ይባላል ።

፪ ፤ ግብፅ ፡ በሰሜን ፡ ከሜዲቴራኒያን ፡ ባሕር ፡ በምሥራቅ ፤ ከቀይ ፡ ባሕር ፤ በደቡብ ፡ ከኖብያ ፤ በምዕራብ ፡ ከምድረ ፡ በዳው ፡ አገር ፡ ይዋሰናል ፡ ነጭ ፡ ዐባይ ፡ በግብፅ ፡ መኻከል ፡ ያደርግና ፡ ከደቡብ ፡ ወደ ፡ ምሥራቅ ፡ ይሄዳል ። የዐባይ ፡ ወንዝ ፡ የሚሞላው ፡ ባመት ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ነው ። በግብፅ ፡ የሚዘንመው ፡ አንድ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ግብፅ ፡ በዚሁ ፡ ለምቶ ፡ ይኖራል ።

፫ ፤ የግብጽ ፡ የመጀመሪያው ፡ ንጉሥ ፡ ሜኒስ ፡ ወይም ፡ ምሥራይም ፡ ነጭ ፡ ዐባይን ፡ ከቀድሞ ፡ መነሻው ፡ ወደ ፡ ጐን ፡ መለሰና ፡ ውሃው ፡ ቀድሞ ፡ ይፈስበት ፡ በነበረው ፡ ላይ ፡ ሜምፊስ ፡ የተባለውን ፡ ከተማ ፡ ቈረቈረ ። ታላቅ ፡ ንጉሥም ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ ሕዝቡ ፡ እንደ ፡ አምላክ ፡ አድርገው ፡ አመለኩት ።

፬ ፤ ሜኒስ ፡ ከነገሠ ፡ በኋላ ፡ የግብፅ ፡ ታሪክ ፡ እጅግ ፡ ግልጽ ፡ ሆኖ ፡ አይታይም ። ከ፪ሺ ፡ ፹፬—እስከ ፡ ፲፰፻፳፭ ፡ ተክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ አገሩ ፡ እንደ ፡ እረኞች ፡ ሆነው ፡ በሚኖሩ ፡ ገገሮች ፡ ይገዛ ፡ ነበር ። ስለዚህ ፡ እረኞች ፡ ነገሥታት ፡ ተብለው ፡ ይጠሩ ፡ ነበር ። በኋላ ፡ ግን ፡ እነዚሁኑ ፡ ነገሥታት ፡ ከግብፅ ፡ አስወጧቸው ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ኒቶክሪስ ፡ የተባለች ፡ አንዲት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሴት ፡ የአገሩ ፡ ንግሥት ፡ ሆነች ። ይህም ፡ የሆነ ፡ ፲፬፻፹፫ ፡ ተክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ ነው ። ወንድሙዋን ፡ ግብፆች ፡ ስለ ፡ ገደሉባት ፡ እሷም ፡ ልትበቀልለት ፡ አሰበች ።

፭ ፤ ንግሥት ፡ ኒቶክሪስ ፡ ለዚሁ ፡ ጕዳይ ፡ ከመሬት ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ ታላቅ ፡ አዳራሽ ፡ አሠራች ። ከዚያም ፡ ታላቅ ፡ ግብር ፡ አዘጋጅታ ፡ የወንድሙዋን ፡ገዳዮች ፡ ወደ ዚሁ ፡ ግብር ፡ ጠራቻቸው ። ግብሩ ፡ በተሰናዳበት ፡ አዳራሽ ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ ፋና ፡ ተበርቶበት ፡ ብርሃኑ ፡ በጣም ፡ ደምቆ ፡ ነበር ። የተጠሩትም ፡ በግብፅ ፡ ግዛት ፡ የታወቁ ፡ ክቡራን ፡ ነበሩ ።

፮ ፤ በገበታው ፡ ለግብር ፡ ተቀምጠው ፡ ሲፈነጥዙ ፡ ለሚመለከተው ፡ በጣም ፡ ደምቆ ፡ የተሟሟቀ ፡ ነበርና ፡ ለማየት ያምር ፡ ነበር ። እንዲሁ ፡ ሆኖ ፡ ሳለ ፡ በድንገት ፡ ከውጪ ፡ በራሳቸው ፡ ላይ ፡ ውኳታና ፡ ፍጅት ፡ ጩኸትም ተነሣ ። (ማየ ፡ አይኅ) ፡ የጥፋት ፡ ውሃ ፡ አዳራሹን ፡ ሰብሮ ፡ ገባ ። ንግሥት ፡ ኒቶክሪስ ፡ አስቀድማ ፡ የወን

ዙን ፡ ውሃ ፡ በምሥጢር ፡ ወደ ፡ አዳራሹ ፡ እንዲገባ ፡ አድርጋ ፡ ነበርና ፡ መብራቱን ፡ ካጠፋ ፡ በኋላ ፡ ውሃው ፡ በዚያ ፡ ታላቅ ፡ ግብር ፡ ላይ ፡ እንዲለቀቅ ፡ አደረገች ። በዚያም ፡ የገቡ ፡ ሁሉ ፡ ሰጥመው ፡ ቀሩ ።

፯ ፤ በግብፅ ፡ ከነገሡት ፡ ሁሉ ፡ ስመ ፡ ጥሩው ፡ ንጉሥ ፡ የነበረው ፡ ሲሶስትሪስ ፡ ነበር ። የነገሠበት ፡ ዘመን ፡ ልኩ ፡ አልታወቀም ። ነገር ፡ ግን ፡ በቀድሞ ፡ ዘመን ፡ በግብፅ ፡ ተሠርተው ፡ በነበሩት ፡ ከተሞች ፡ ፍራሽ ፡ ውስጥ ፡ ከተሠራ ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ የሚሆነው ፡ አንድ ፡ የተጠረበ ፡ ድንጋይ ፡ ተገኘ ። ይህንም ፡ የሱ ፡ ምስል ፡ ይመስላል ። ግን ፡ እጅግ ፡ ያረጀ ፡ ምስል ፡ መኖሩ ፡ ያጠራጥራል ፤ ይህ ፡ ንጉሥ ፡ ዓለምን ፡ ለማሸነፍ ፡ አስቦ ፡ ከግብፅ ፡ ሲነሣ ፡ የሚሊዮን ፡ እኩሌታ ፡ የሚሆኑ ፡ እግረኞች ፡ ወታደሮች ፡ ፳፬ ፡ ሺሕ ፡ ፈረሰኞች ፡ ፳፯ ፡ ሺሕ ፡ የተሰናዱ ፡ ሠረገሎች ፡ ነበሩት ።

፰ ፤ ዝና ፡ ፈላጊነቱ ፡ በክብር ፡ ተፈጸመለትና ፡ ትልቅ ፡ ድል ፡ አገኘ ። በየሄደበት ፡ ስፍራ ፡ ሁሉ ፡ ከእብነ ፡ በረድ ፡ የተሠራ ፡ ሐውልት ፡ አቆመ ። የሚመጣው ፡ ትውልድ ፡ እንዳይረሳው ፡ በቆመው ፡ ሐውልት ፡ ላይ ፡ ጽሕፈት ፡ እንዲቀረጽበት ፡ አደረገ ። በብዙዎቹ ፡ ሐውልት ፡ ላይ ፡ እንዲህ ፡ የሚል ፡ ቃል ፡ ተጽፎአል ።

፱ ፤ (ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ሲሶስትሪስ ፡ በጦር ፡ ሠራዊቱ ፡ ኀይሉ ፡ ይህን ፡ አገር ፡ አሸንፎዋል) ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ሐውልቱ ፡ ወድቆ ፡ ተሰባብሮ ፡ አቧራ ፡ ሆኖ ፡ ይሆናል ። ወይም ፡ ከመሬት ፡ ውስጥ ፡ ተቀብሮ ፡ ይሆናል ። የሲሶስትሪስ ፡ ታሪክ ፡ እጅግ ፡ ግልጥ ፡ ሆኖ ፡ አይታይም ። አንድ ፡ አንዶች ፡ ታሪክ ፡ ጸሐፊዎች ፡ እንደዚህ ፡ አላደረገም ፡ ብለው ፡ ይጠራጠራሉ ።

፲ ፤ ሌሎች ፡ ታሪክ ፡ ጸሐፊዎች ፡ ደግሞ ፡ ከጦርነቱ ፡ ሲመለስ ፡ ልክ ፡ የሌለው ፡ ምርኮ ፡ ማርኮ ፡ ብዙ ፡ ግመሎች ፡ የከበረ ፡ ዕቃ ፡ እንደ ፡ ተጫኑ ፡ አምጥቶ ፡ ከዚያ ፡ በኋላ ፡ እጅግ ፡ ያማረ ፡ ቤተ ፡ ጣዖትና ፡ የውሃ ፡ መንገድ ፡ እንዳሠራ ፡ ያረጋግጡልናል ።

፲፩ ፤ ሲሶስትሪስ ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ጣዖት ፡ ሊሰግድ ፡ በሄደ ፡ ጊዜ ፡ የተቀመጠበትን ፡ ሠረገላ ፡ የሚጐትቱ ፡ በምርኮ ፡ የመጡ ፡ ነገሥታት ፡ ናቸው ። እንደ ፡ ፈረስ ፡ ተጠምደው ፡ አራት ፡ ሆነው ፡ እንዲስቡ ፡ ተደርጓል ። ሠረገላውን ፡ ሲስቡ ፡ ሳሉ ፡ ልብሰ ፡ መንግሥታቸው ፡ በቧራ ፡ ላይ ፡ ይጐተታል ። ዳሩ ፡ ግን ፡ እያደር ፡ ትዕቢተኛው ፡ ሲሶስትሪስ ፡ አርጅቶ ፡ ዕዉር ፡ ሆነ ። ሠረገላውን ፡ የሚስቡትን ፡ የማረካቸውን ፡ ነገሥታት ፤ ወይም ፡ ከጫማው ፡ ሥር ፡ ወድቀው ፡ የሚሰግዱለትን ፡ ለማየት ፡ አልቻለም ፤ ጭራሽ ፡ የሚያሳዝን ፡ ሆኖ ፡ በመጨረሻው ፡ ራሱን ፡ ገድሎ ፡ሞተ ።

## ጥያቄ ።

፩ ፤ የአፍሪካ ፡ ሕዝብ ፡ የማን ፡ ዘር ፡ ናቸው ፡ ? የግብፅን ፡ መንግሥት ፡ የመሠረተው ፡ ማነው ፡ ?
የተመሠረተበት ፡ ዘመን ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ ? ስለ ፡ ሜኒስ ፡ ምን ፡ ይታሰባል ፡ ?

፪ ፤ የግብፅ ፡ ወሰን ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ? ነጭ ፡ ዐባይ ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ? በግ

LAPSLEY / BROOKS FOUNDATION, INC.
1701 N. GREENVILLE AVE. ST. 810
RICHARDSON, TEXAS 75081, USA

ብፅ ፡ ሁልጊዜ ፡ ይዘንግልን ፡ ?

፫ ፤ ሜምፊስ ፡ የተሠራው ፡ መቼ ፡ ነው ፡ ? ማን ፡ ሠራው ፡ ? ስለ ፡ ሜኒስ ፡ ምን ፡ ይባላል ፡ ?

፬ ፤ የግብፅ ፡ ታሪክ ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ? እረኞች ፡ ነገሥታት ፡ የተባሉት ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ?
ንግሥት ፡ ኒቶክሪስ ፡ ምን ፡ አደረገች ፡ ?

፭ ፤ ስለ ፡ ወንድሙዋ ፡ ሞት ፡ እንደምን ፡ አድርጋ ፡ ደመኛዋን ፡ ተበቀለች ፡ ?

፮ ፤ ስለ ፡ ሲሶስትሪስ ፡ ምን ፡ ትላለህ ፡ ? የጦር ፡ ሠራዊቱ ፡ እንዴት ፡ ነበር ፡ ?

፯ ፡ ሲሶስትሪስ ፡ ባቆማቸው ፡ ሐውልቶች ፡ ምን ፡ ተጽፎባቸው ፡ ነበር ፡ ? እስከ ፡ ዛሬ ፡ ሐውልቶቹ ፡ እንደ ፡ ተተከሉ ፡ ናቸውን ፡ ? አንዳንዶች ፡ ጸሐፎች ፡ ስለምን ፡ ይጠራጠሩባቸዋል ፡ ?

፰ ፤ ሌሎች ፡ ምን ፡ ይላሉ ፡ ?
የሲሶስትሪስ ፡ ሠረገሎች ፡ የሚነዱት ፡ እንዴት ፡ ነበር ፡ ?
የዚህ ፡ የሚያሳዝን ፡ ንጉሥ ፡ ዕድል ፡ መጨረሻው ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ?

## ም ዕ ራ ፍ ፡ ፵ ፡ አ ፍ ሪ ካ ።

የግብፃውያን ፡ የቤት ፡ ሥራ ፡ አሠራር ፡ ዕውቀትና ፡ የደንጊያ ፡ መውቀር ፡ ብልሀት ።

፩ ፤ ግብፆች ፡ የቀድሞ ፡ ታሪካቸው ፡ በጣም ፡ ግልጽ ፡ ሆኖ ፡ አይታይም ። ተረት ፡ የመሰለት ፡ የሚያስደንቅ ፡ ታሪካቸውን ፡ ስንሰማው ፡ ፈጽሞ ፡ ወደ ፡ ጥርጥር ፡ የሚያደርስ ፡ ይመስላል ። ነገር ፡ ግን ፡ የሚያሥቅ ፡ ታሪክ ፡ ተናጋሮችንና ፡ የታላላቅ ፡ ከተሞች ፡ ፍራሽን ፤ እስከ ፡ ዛሬ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ስፍሮች ፡ የሚገኙትን ፡ ትንንሾች ፡ ነገሮች ፡ ስንመለከት ፡ ወደ ፡ እምነት ፡ ያደርሱናል ። ከሦስትና ፡ ከራት ፡ ሺሕ ፡ ዓመት ፡ በፊት ፡ ብዙ ፡ ሚሊዮን ፡ ሕዝብ ፡ እንደ ፡ ነበሩ ፡ እጅግ ፡ ለዐይን ፡ ያማሩ ፡ ታላላቅና ፡ ሰፋፊ ፡ የነበሩ ፡ የከተሞቻቸው ፡ ፍራሽ ፡ በመገኘታቸው ፡ እንረዳለን ።

፪ ፤ በጥንቱም ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ በዛሬው ፡ አስተያየት ፡ ስንገምተው ፡ እጅግ ፡ ደምቆ ፡ የሚታይ ፡ ከተማ ፡ እንደ ፡ ቴቤስ ፡ ያለ ፡ አይገኝም ። ባለመቶ ፡ በር ፡ ከተማ ፡ ይሉታል ። በጦር ፡ ጊዜ ፡ ከዚህ ፡ ከተማ ፡ በያንዳንዱ ፡ በር ፡ የሚወጣው ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ እንደሚከተለው ፡ ነው ። መማሪያቸው ፡ የተሰናዳ ፡ ፪፻ ፡ ሠረገሎችና ፡ ፪ ፡ ሺሕ ፡ ወታደሮች ፡ ናቸው ።

፫ ፤ ከ፪ሺ.፬፻ ፡ ዓመት ፡ በፊት ፡ የነበረ ፡ ካምቢሲስ ፡ የተባለ ፡ የፋርስ ፡ ንጉሥ ፡ በነበረበት ፡ ዘመን ፡ ቴቤስ ፡ ፈርሶ ፡ ነበር ። የከተማው ፡ ፍራሽ ፡ ከነጭ ፡ ዐባይ ፡ ወንዝ ፡ ግራና ፡ ቀኝ ፡ ፳፮ ፡ ማይል ፡ ርቀት ፡ ተበታትኖ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ይታያል ። ከሐውልቱም ፡ ያያሎቹ ፡ ውፍረት ፡ ፲፪ ፡ ሬት ፡ ይሆናል ።

፬ ፤ ከግብፆች ፡ ነገሥታት ፡ አንደኛው ፡ ዙሪያው ፡ አርባ ፡ አምስት ፡ ማይል ፡ የሚ
ሆን ፡ ትልቅ ፡ ጕድጓድ ፡ ቆፍራችሁ ፡ ወደታች ፡ ጥልቅነት ፡ ያለው ፡ ባሕር ፡ ይሁን ፡
ብሎ ፡ ሕዝቡን ፡ አዘዛቸው ። አንደኛው ፡ ንጉሥ ፡ ደግሞ ፡ ከመሬት ፡ ውስጥ ፡
አስቆፍሮ ፡ ከዕብነ ፡ በረድ ፡ የታነጸ ፡ ሦስት ፡ ሺሕ ፡ ጓዳ ፡ ያለው ፡ አዳራሽ ፡
አሠራ ። ለዚህም ፡ ዘወርዋራ ፡ መንገድ ፡ ነበረው ።
፭ ከፍ ፡ ባለው ፡ ጓዳ ፡ አንዲት ፡ የተቀደሰች ፡ አዞና ፡ ግብፆችም ፡ የሚያመልኩ
ዋቸው ፡ ሌሎች ፡ አራዊት ፡ ነበሩ ። ከምድር ፡ በታች ፡ ባለው ፡ ጓዳ ፡ የግብፃው
ያን ፡ ነገሥታት ፡ ፀዕም ፡ ተጋድሞአል።
፮ ፤ ደግሞ ፡ አንድ ፡ የሚያስደንቀው ፡ ሥራ ፡ መሬቱን ፡ ወደ ፡ ውስጥ ፡ ቆፍረው ፡
አለቱ ፡ ሲወጣ ፡ ያንን ፡ ወቅረው ፡ የደንጊያ ፡ ምሰሶ ፡ ያደርጉታል ። ውስጥ ፡ ለው
ውስጥ ፡ (ጋሌሪ ፡ የደርብ ፡ መንገድ ፡ እያደረጉ ፡ ይሠሩታል ። በዚህ ፡ ውስጥ
ከሺሕ ፡ ዓመት ፡ በፊት ፡ የሞተውን ፡ ሰው ፡ ሬሳ ፡ አጋድመውት ፡ ይገኛል ። ሳይለ
ወጥ ፡ ልክ ፡ እንደ ፡ ተቀበረ ፡ ጊዜ ፡ ሆኖ ፡ ይታያል ። ይህንንም ፡ ሙሚስ ፡ ይሉታል ።
፯ ፤ የግብፅ ፡ ፒራሚድ ፡ ሲባል ፡ የማያውቅ ፡ ሰው ፡ የለም ፤ ይህም ፡ ትልቅ ፡ ሥራ ፡
በነጭ ፡ ዐባይ ፡ ወንዝ ፡ ዳር ፡ ይገኛል። ታላቁ ፡ ፒራሚድ ፡ ከፍታው ፡ ፭፻ (ሜማ)ፊት ፡ ነው።
፰ ፤ የግብፅ ፡ ፒራሚዶች ፡ የተሠሩበትን ፡ ዘመን ፡ የሠራቸውም ፡ ሰው ፡ ማን ፡ እን
ደሆነ ፡ ከቶ ፡ አይታወቅም ። ለመሆኑ ፡ ግን ፡ ለመቃብራቸውና ፡ ለዘለዓለም ፡
መታሰቢያ ፡ እንዲሆኑዋቸው ፡ ጥንታውያን ፡ የግብፅ ፡ ነገሥታት ፡ አሠርተዋቸዋል ፡
ይባላል ። ነገር ፡ ግን ፡ ፒራሚዱ ፡ ሳይፈርስና ፡ ሳይናድ ፡ ምንም ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡
ቢቈይ ፡ የሠሩት ፡ ነገሥታት ፡ እነማን ፡ እንደ ፡ ሆኑ ፡ ስማቸው ፡ ተረስቷል ።
፱ ፤ በቴቤስ ፡ አጠገብ ፡ ባንድ ፡ ሜዳ ፡ ላይ ፡ ወንድና ፡ ሴት ፡ ሆነው ፡ የሰው ፡ መልክ
የሚመስሉ ፡ ሁሉ ፡ ታላላቅ ፡ ሐውልቶች ፡ አሉ ፤ ቁመታቸው ፡ ፶ ፡ ፊት ፡ ይሆናል ፡
ለሚመለከታቸው ፡ ያስደንቃሉ ።
፲ ፤ በግብፆች ፡ መኻከል ፡ ከሚገኘው ፡ ከቀድሞ ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ በጣም ፡ የሚያስደ
ንቅ ፡ ሲፊክስ ፡ የሚሉት ፡ ነገር ፡ ፡ ነው ። ይኸውም ፡ ከታች ፡ አካሉ ፡ የአንበሳ ፡ ሆኖ ፡
ከላይ ፡ ከራሱ ፡ ትልቅ ፡ የሴት ፡ መልክ ፡ ነው።ዛሬ ፡ እንደሚታየው ፡ ከታች ፡ ያለው ፡
አካሉ ፡ በአሸዋ ፡ ውስጥ ፡ ተቀብሯል ። የላይኛው ፡ ክፍል ፡ ከምድር ፡ በላይ ፡ የሚ
ታየው ፡ ራሱና ፡ አንገቱ ፡ ነው ። ይኸውም ፡ ቁመቱ ፡ ሰባ ፡ ፊት ፡ ነው ። የተጠረ
በው ፡ ከአለት ፡ ደንጊያ ፡ ነው ። በሩቁ ፡ ለተመለከተው ፡ ሰው ፡ አፍንጫዋ ፡ ደፍ
ጣጣ ፡ የሆነች ፡ ሴት ፡ ከአሸዋ ፡ ውስጥ ፡ ብቅ ፡ ያለች ፡ ይመስላል ።
፲፩ ፤ በጥንት ፡ ቴቤስ ፡ አጠገብ ፡ ያለው ፡ ሉክሶር ፡ የተባለው ፡ ከተማ ፡ ፍራሽ ፡ ለተ
መልካቹ ፡ የሚያስደንቅ ፡ ሁኖ ፡ ያለመጠን ፡ ትልቅ ፡ ነው ። ከመቅደሶቹ ፡ አንዱ
የጥንት ፡ ሥራ ፡ ስመ ፡ ጥሩ ፡ ይመስላል ።
፲፪ ፤ ግብፃውያን ፡ ይህን ፡ የሚያስደንቅ ፡ ሥራ ፡ ሲሠሩበት ፡ በነበሩ ፡ ዘመን ፡ ከዛሬ
ይልቅ ፡ የዚያን ፡ ጊዜ ፡ ብዙ ፡ ጥበብ ፡ ዐዋቂዎችና ፡ የተማሩ ፡ ሰዎች ፡ እንደነበሩ ፡

ይታያል ። ጥበባቸውና ፡ ዕውቀታቸው ፡ ከፍ ፡ ያለ፡እንደ ፡ ነበረ ፡ ተመልክተው ፡ የሌሎች ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ እንደ ፡ አስግተኞች ፡ ይገምቱዋቸው ፡ ነበር ።

፲፫ ፡ ግብፆች ፡ ልማደ ፡ አገር ፡ ከንቱ ፡ አምልኮት ፡ ነበራቸው ። ዋናዪቱም ፡ ጣዖታቸው ፡ ኢሲስ ፡ ትባላለች ፤ ባልዋም ፡ ኦሲሪስ ፡ ይባላል ። ምስላቸውን ፡ ሠርተው ፡ ለነዚህ ፡ ይሰግዱላቸዋል ። ኢሲስ ፡ በጣም ፡ የተከበረች ፡ ጣዖት ፡ ናት ፤ ሕዝቡም አያሎች ፡ መቅደሶች ፡ ሠርተውላታል ፤ በዚህም ፡ ያመልኩዋታል ።

## ጥያቄ ።

፩ ፡ የግብፅ ፡ ጥንተ፡ታሪኩ ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ?የከተማው ፡ ፍራሾችና፡ የቆሙትን ፡ ሐውልቶች ፡ የሠራ ፡ ማን ፡ ኑሩዋል ፡ ?

፫ ፤ ምን ፡ ያሳያሉ፡ ? ቴቤስ ፡ እንዴት ፡ ሆነ፡ ? ሕዝቡ ፡ እንደምን ፡ ሆኑ ፡ ? ቴቤስን ፡ ያጠፋ ፡ ማነው ፡ ? ፍራሹና ፡ ሕንጻው ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ?

፬ ፤ ጥቂቶች ፡ ነገሥታት፡ የሠሩትን ፡ ተናገር ፤ ግለጽ ፤ ዘወርዋራ ፡ መንገድ የተባለው ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ?

፭ ፤ በዚሁ፡ዘወርዋራ፡መንገድ ፡ ምን ፡ ተደርጎበታል ፡ ? በምድር፡ውስጥ፡ስለሚሠራ ፡ ሕንጻ ፡ ተናገር ። ሙሚስ ፡ የተባሉት ፡ ምንድር ፡ ናቸው ፡ ?

፰ ፤ ፒራሚድ ፡ የተባሉት፡ምንድር ፡ ናቸው፡ ? የተሠሩበት፡ምክንያት፡ለምን፡ ይሆን፡? በቴቤስ ፡ አጠገብ ፡ የቆመ፡ መታሰቢያ ፡ የማነው ፡ ? ከድንጊያ፡ተቀርፆ ፡ ስለ ፡ ተሠራው ፡ ምስል ፡ ተናገረ ።

፲፩ ፤ የሉክስር ፡ ፍራሽ ፡ ማነው ፡ ?

፲፪ ፤ እኛ ፡ በምንናገርበት ፡ ዘመን ፡ ግብፃውያን ፡ እንዴት ፡ ናቸው ፡ ? በሌሎች ፡ አገር ፡ ሕዝብ ፡ ዐይን ፡ ምን ፡ መስለው ፡ ይታያሉ ፡ ?

፲፫ ፤ የግብፆች ፡ ከንቱ ፡ አምልኮት፡እንዴት፡ነው ፡ ?ኢሲስና ፡ ኦስሪስ፡የተባሉ፡ ጣዖቶቻቸው ፡ ምን ፡ አደረጉላቸው ፡ ?

## ምዕራፍ ፡ ፺፩ ፡ አፍሪካ ።

### ስለ ፤ ጵቶልሚዮስና ፡ ስለ ፡ ንግሥት ፡ ክሌዎፓትራ ።

፩ ፤ ስለ ፡ አይሁድ ፡ ታሪክ ፡ በግብፅ ፡ ዐባርነት ፡ እንደ ፡ ነበሩና ፡ በተአምራት ፡ እንዴት እንዳመለጡ፡ ተናግሬአለሁ ። በኋላ ፡ ሺሻክ ፡ የተባለ ፡ የግብፅ ፡ ንጉሥ፡ ኢየሩሳሌምን ፡ ስለ ፡ ያዛት ፡ የሰሎሞን ፡ ቤተ፡መቅደስ፡በዝብዞ ፡ ንዋየ ፡ ቅድሳቱን ፡ ሁሉ ጠርጎ ፡ ወሰደው ።

፪ ፤ አሚኖፊስ ፡ የተባለ፡ስመ፡ጥሩ ፡ የግብፅ ፡ ንጉሥ ፡ ነበር ፤ ይህም፡ምናልባት ፡ ለስሙ ፡ መጥሪያ፡ (ለመታሰቢያው) ብሎ ፡ አንድ ፡ ትልቅ ፡ መቅደስና ፡ ምስል ፡ ያቆመ ፡ ሜምኖን፡የተባለው ፡ ንጉሥ ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም ። የዚህም ፡ ፍራሽ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ በቴቤስ ፡ ይታያል ።ያቆመውም ፡ የድንጊያ ፡ ምስል ፡ ዐሓይ ፡ ስት

ወጣ ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ ቃል ፡ ፀሓይ ፡ ስትጠልቅ ፡ የኀዘን ፡ ቃል ፡ ያሰማል ፡ ይባላል ፡ ዛሬም ፡ በዚያ ፡ የሚያልፉ ፡ መንገደኞች ፡ ድምፁን ፡ የሚሰሙ ፡ ይመስላቸዋል ።

፫ ፤ ፭፻፳፭ ዓመት ፡ ከዘመነ ፡ ክርስትና ፡ በፊት ፡ ካምቢሲስ ፡ ንጉሠ ፡ ፋርስ ፡ ግብፅን ፡ ድል ፡ አድርጎ ፡ ነበረና ፡ ሳሜኒቱስ ፡ የተባለውን ፡ የግብፅን ፡ ንጉሥ ፡ የወይፈን ፡ ደም ፡ ብግድ ፡ ስለ ፡ አስጠጣው ፡ እንደ ፡ መርዝ ፡ ሆነበትና ፡ በዚሁ ፡ ጠንቅ ፡ ሞተ ።

፬ ፤ ሦስት ፡ መቶ ፡ ሠላሳ ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ ከዘመነ ፡ ክርስትና ፡ በፊት ፡ የመቄዶን ያው ፡ ንጉሥ ፡ ታላቁ ፡ እስክንድር ፡ ግብፅን ፡ ድል ፡ አድርጎት ፡ ነበር ። በዚህ ፡ ስፍራ ፡ እስክንድርያ ፡ የተባለ ፡ አንድ ፡ ስመ ፡ ጥሩ ፡ ከተማ ፡ ሠራ ። ይህም ፡ ከተማ ፡ በዓለም ፡ ከታወቁት ፡ ከተሞች ፡ እጅግ ፡ ጥሩ ፡ ሆኖ ፡ የተሠራና ፡ መሰል ፡ የሌለው ፡ አያል ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ የቄየ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ መሆኑ ፡ ታውቆዋል ። የጥንቱ ፡ ሥራው ፡ ፈራርሶ ፡ ዛሬ ፡ የሚታየው ፡ እስክንድርያ ፡ ኢጥ ንቱ ፡ በጣም ፡ ያነሰ ፡ ነው ።

፭ ፤ እስክንድር ፡ ሲሞት ፡ በዚሁ ፡ በእስክንድርያ ፡ ተቀበረ ። ይኸው ፡ ከተማ ፡ ስመ ፡ ጥሩ ፡ በመሆኑ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ በግብፅ ፡ ዋና ፡ የንግድ ፡ ሁለተኛ ፡ ከተማ ፡ ተብሎ ፡ ይጠራል ።

፮ ፤ እስክንድር ፡ የሱ ፡ ጄኔራል ፡ የነበረውን ፡ ጵቶልሚዎስን ፡ አገሩን ፡ እንዲገዛ ፡ ሾመው ። ከጵቶልሚዎስ ፡ ጀምሮ ፡ ተወላጆቹ ፡ ሁሉ ፡ የንጉሥ ፡ ዘር ፡ ተብለው ፡ ሁሉም ፡ ጵቶልሚዎስ ፡ ተብለዋል ። ፪፻፺፬ ፡ ዓመት ፡ ገዝተዋል ። ከነዚህም ፡ በመ ጨረሻ ፡ የነገሠው ፡ ጵቶልሚዎስ ፤ ዲዮናስዮስ ፡ ይባላል ። በላዩ ፡ የገዛ ፡ ሚስቱ ፡ ተነሥታ ፡ ሸፈተችበትና ፡ ተዋጋችው ። ጵቶልሚዎስ ፡ ዲዮናስዮስ ፡ በመጨረሻ ፡ ድል ፡ ሆነና ፡ ለማምለጥ ፡ የማይሆንለት ፡ ቢሆን ፡ በነጭ ፡ ዐባይ ፡ ወንዝ ፡ ውስጥ ፡ ገብቶ ፡ ሰጠመ ። ሚስቱ ፡ ክሌዎፓትራ ፡ የተባለች ፡ የግብፅ ፡ ዋና ፡ ገዢ ፡ ሆነች ።

፯ ፤ አሉ ፡ ተብለው ፡ ከሚጠሩት ፡ ቈንጆጅት ፡ አንዲቱ ፡ እርስዋ ፡ ነበረች ። ስጦ ታዋና ፡ ተፈጥሮዋ ፡ ከውበትዋ ፡ ጋር ፡ የተካከሉ ፡ ነበሩ ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ክፉ ፡ ነበረች ። ከሠራችው ፡ ሁሉ ፡ እጅግ ፡ የሚያስቀቅው ፡ ነገር ፡ ያሥራ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ሕፃን ፡ የነበረውን ፡ የገዛ ፡ ወንድምዋን ፡ በመርዝ ፡ ማስገደልዋ ፡ ነው ። ምንም ፡ ክፋትዋን ፡ ዓለም ፡ ቢያውቀው ፡ እኔ ፡ ነኝ ፡ ያለ ፡ ጀግና ፡ የውበት ፡ ማጥመጃዋን ፡ ሊቃወም ፡ የሚችል ፡ አልተገኘም ።

፰ ፤ ማርክ ፡ አንቶኒ ፡ የተባለ ፡ የሮም ፡ ጄኔራል ፡ በግሪክ ፡ አገር ፡ ፊሊጵ ፡ በተ ተባለች ፡ አውራጃ ፡ ብርቱስንና ፡ ካሲውስን ፡ ድል ፡ ባደረገ ፡ ጊዜ ፡ ከሜዴቴራ ኒያን ፡ ባሕር ፡ በሰሜን ፡ ምሥራቅ ፡ ወደምትሆን ፡ ወደ ፡ ሲሲሊያ ፡ እንድትመጣ ፡ ክሌዎፖትራን ፡ አስጠራት ። ምክንያቱም ፡ ለቡርቱስ ፡ ረድታ ፡ ነበርና ፡ ሊቀጣት ፡ አስቦ ፡ ነበር ።

፱ ፤ ክሌዎፓትራ ፡ ጥሪው ፡ እንደ ፡ ደረሳት ፡ እሺ ፡ ብላ ፡ በፍጥነት ፡ ተነሥታ ፡ በተ ለይ ፡ በወርቅ ፡ ባጌጠ ፡ ታንኳ ፡ ገባች ። ታንኳው ፡ በሸራው ፡ ፈንታ ፡ ዋጋው ፡ የበዛ ፡ የከበረ ፡ ሐር ፡ ነበረው ። ታንኳውን ፡ በብር ፡ መቅዘፊያ ፡ የሚቀዝፉት ፡ የተወደዱ ፡ ቈንጆጅት ፡ ነበሩ ።

፲ ፡ ንግሥት ፡ ክሌዎፓትራ ፡ ሐር ፡ ተጋርዶላት ፡ በመርከቡ ፡ ተደግፋ ፡ ተቀምጣ ፡ ነበረች ። እንደዚህ ፡ ሁና ፡ ሲድኑስ ፡ በተባለው ፡ ወንዝ ፡ ተንሳፈፈች ። ያለችበትም ፡ ቃንኳ ፡ እጅግ ፡ ያማረ ፡ ነበር ። እርስዋም ፡ ራስዋ ፡ የተወደደች ፡ ነበረች ። የሚታየው ፡ ሁሉመናዋ ፡ ሕልም ፡ ይመስል ፡ ነበር ።

፲፩ ፡ ከታንኳው ፡ መጋረጃ ፡ ነፋስ ፡ እየጠቀሰ ፡ የሚወስደው ፡ ሽቱ ፡ እያወደ ፡ ክሌዎፓትራ ፡ እንደ ፡ ተቃረበች ፡ ማርክ ፡ አንቶኒን ፡ አስጠነቀቀው ። ከሩቅ ፡ ልብ ፡ የሚነካ ፡ የሙዚቃ ፡ ድምፅ ፡ ይሰማ ፡ ነበር ። ቀጥሎ ፡ የብር ፡ መቅዘፊያው ፡ ሲብለጨለጭ ፡ ከሩቅ ፡ ይታይ ፡ ነበር ።

፲፪ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ አንቶኒ ፡ የግብፆችን ፡ ንግሥት ፡ በተመለከተ ፡ ጊዜ ፡ ምንም ፡ አላሰበም ። ማርክ ፡ አንቶኒ ፡ ተክሌዎፓትራ ፡ እስኪገናኝ ፡ ድረስ ፡ ክቡር ፡ ሰውና ፡ ጀግና ፡ መሆኑን ፡ አሳየ ፡ እንጂ ፡ ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ ፍጹም ፡ እንደበሪያዋ ፡ ሆነ ።

፲፫ ፡ ተክሌዎፓትራና ፡ ከርሱ ፡ ከፉ ፡ አካሄድ ፡ የተነሣ ፡ አክታቢዎስ ፡ ከተባለ ፡ ከሌላ ፡ የሮም ፡ ጀኔራል ፡ ጋር ፡ በግሪክ ፡ አገር ፡ አክቲውም ፡ በተባለች ፡ አውራጃ ፡ ላይ ፡ ተዋግተው ፡ አንቶኒ ፡ ድል ፡ ሆነና ፡ በገዛ ፡ ሰይፉ ፡ ወድቆ ፡ ሞተ ። ክሌዎፓትራም ፡ አክታቢዎስ ፡ በሕይወትዋ ፡ ወደ ፡ ሮም ፡ የወሰዳት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በሕዝብ ፡ መኻከል ፡ እንደሚያጋልጣት ፡ ተረዳችው ።

፲፬ ፡ ስለዚህ ፡ ለመታገሥ ፡ የማይቻል ፡ ሲሆንባት ፡ ጊዜ ፡ በግብፅ ፡ አገር ፡ አንድ ፡ ዐይነት ፡ በትናከስ ፡ ጊዜ ፡ ሕማሙ ፡ የማይሰማ ፡ መርዛም ፡ እባብ ፡ ስላለ ፡ ክሌዎፓትራ ፡ ከንደዚህ ፡ ያለ ፡ መርዛም ፡ እባብ ፡ አንዱን ፡ አሲዛ ፡ አስመጥታ ፡ ሰውነቷን ፡ አስነከሰች ። ትንሽ ፡ ቈይታ ፡ ሁለመናዋ ፡ ደነዘዘ ፡ አበጠ ፡ ወዲያው ፡ ልቡዋ ፡ መምታቱን ፡ አቆመ ። ውብት ፡ የነበራት ፡ ክፉዒቱ ፡ የግብፅ ፡ ንግሥት ፡ ክሌዎፓትራ ፡ እንደዚህ ፡ ሆና ፡ ሞተች ። ይህም ፡ የሆነው ፡ ተክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ ሠላሳ ፡ ዓመት ፡ ነው ።

፲፭ ፡ የንግሥት ፡ ክሌዎፓትራ ፡ ታሪክ ፡ ታላቅ ፡ ትምህርት ፡ ያለው ፡ ነው ። ሰው ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ታላቅ ፡ የሀብት ፡ ዕድልና ፡ ስጦታ ፡ ከገኘ ፡ በኋላ ፡ ለበጎ ፡ ነገር ፡ ባያውለው ፡ ለጕዳት ፡ ይሆንበታል ።

## ጥያቄ ።

፩ ፡ ሺሻክ ፡ ማነው ፡ ? ምን ፡ አደረገ ፡ ?
፪ ፡ አሜኖፊስ ፡ ማነው ፡ ?
የሚመኖስ ፡ ሐውልት ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ?
፫ ፡ ግብፆችን ፡ ድል ፡ ያደርጋቸው ፡ ማነው ፡ ?
ድል ፡ የሆኑትስ ፡ መቼ ፡ ነው ፡ ?
ያልታደለ ፡ ሳምኒቱስ ፡ ምን ፡ ሆነ ፡ ?
፬ ፡ እስክንድር ፡ ግብፅን ፡ ያሸነፈው ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ ?

፮ ፤ ጽቶልሚዮስና ፡ ተወላጆቹ ፡ እንዴት ፡ ሆኑ ፡ ?
በግብፅ ፡ ስንት ፡ ዘመን ፡ ነገሡ ፡ ?
ጽቶልሚዮስ ፡ ዲዮናስዮስ ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ?
፯ ፤ ሚስቱ ፡ ማነች ፡ ?
ክሌዎፓትራ ፡ እንዴት ፡ ሆነች ፡ ?
እንደምን ፡ ያለ ፡ ክፋት ፡ አደረገች ፡ ?
ክሌዎፓትራን ፡ ወደዚህ ፡ ነገር ፡ ያደረሳት ፡ ምንድነው ፡ ?
፰ ፤ ማርክ ፡ አንቶኒ ፡ የተባለ ፡ ማነው ፡ ?
ክሌዎፓትራን ፡ ሊቀጣት ፡ የፈለገ ፡ ስለምንድነው ፡ ?
ክሌዎፓትራ ፡ ወደሲሲል ፡ የደረሰችበት ፡ አሳብ ፡ ምንድነው ፡ ተናገር ።
፲፪ ፤ አንቶኒ ፡ ተክሌዎፓትራ ፡ እስኪገናኝ ፡ ድረስ ፡ አሳቡ ፡ ምንድን ፡ ነበር ፡ ?
፲፫ ፤ አንቶኒ ፡ ድል ፡ የሆነው ፡ የት ፡ ላይ ፡ ነው ፡ ?
አክታቢዎስ ማነው ፡ ?
አንቶኒ ፡ በመጨረሻው ፡ ምን ፡ ሆነ ፡ ?
ክሌዎፓትራ ፡ በመጨረሻው ፡ ራስዋን ፡ መግደል ፡ የተመኘች ፡ ስለምንድነው ፡ ?
፲፬ ፤ በምን ፡ ሞተች ፡ ?
ይህ ፡ የሆነው ፡ ተክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ በስንት ፡ ዘመን ፡ ነው ፡ ?

## ምዕራፍ ፡ ፵፪ ፡ አፍሪካ ።

### የግብፆችን ፡ ታሪክ ፡ የሚከተል ።

፩ ፤ ከንግሥት ፡ ክሌዎፓትራ ፡ ሞት ፡ በኋላ ፡ ግብፅ ፡ ለሮም ፡ መንግሥት ፡ ተገዛና ፡ እስከ ፡ ዘመነ ፡ ክርስትና ፡ ፮፻፵ ፡ ዓመት ፡ ድረስ ፡ የምሥራቅ ፡ መንግሥት ፡ እየተ ባለ ፡ ለሮም ፡ እንደ ፡ ተገዛ ፡ ቈየ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሳራሲኖች ፡ ድል ፡ አደረጉትና ፡ እስከ ፡ ፮፻ ፡ ዓመት ፡ ቈየ ።

፪ ፤ የሳራሲን ፡ ገገሮች ፡ ያሠለጠኗቸው ፡ ማምሉክስ ፡ የተባሉት ፡ የገዛ ፡ ዘበኞቻቸው ፡ ሳራሲኖችን ፡ ተዘፋናቸው ፡ ዘርጥጠው ፡ አወረዱቸው ፡ ቱርክ ፡ መጥቶ ፡ ድል ፡ እስኪ ያደርጋቸው ፡ ድረስ ፡ ማምሉኩስ ፡ ግብፅን ፡ እስከ ፡ ሺ ፡ ፭፻፲፯ ፡ ገዝቷል ። ቱርኮችም ፡ ግብፅን ፡ እስከ ፡ ሺ ፯፻፺፰ ፡ ዓመት ፡ ገዝተዋል ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ናፖሊዮን ፡ ቦናፓርቴ ፡ አርባ ፡ ሺሕ ፡ የሚሆን ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ከፈረንሳይ ፡ አገር ፡ አምጥቶ ፤ ግብፅን ፡ ወረረው ።

፫ ፤ ቱርኮችም ፡ ግብፅን ፡ ከያዙ ፡ ወዲህ ፡ ማምሉክስ ፡ የተባለውን ፡ ጭፍራ ፡ ወደ ፡ ሥራቸው ፡ አግብተው ፡ ጠብቀውት ፡ ነበርና ፡ እነዚህ ፡ ተስፉ ፡ እስኪቈርጡ ፡ ድረስ ፡ ተከላከሉ ። ጦርነቱን ፡ የሚዋጉበት ፡ ስፍራ ፡ በፒራሚዱ ፡ አጠገብ ፡ ነበር ። በዚያ ፡ ሲዋጉ ፡ ሳሉ ፡ እኩሌቶቹ ፡ እዚያው ፡ ታረዱ ። ሌሎቹም ፡ እየዘለሉ ፡ ወደ ፡ ነጭ ፡ ዐባይ ፡ ወንዝ ፡ ባሕር ፡ ሰጠሙ ። ከዚህ ፡ ጦርነት ፡ በኋላ ፡ ናፖሊ

ዮን ፣ ቶሎ ፣ ብሎ ፣ ወዲያው ፣ ወደ ፣ ፈረንሳይ ፣ አገር ፣ ተመለሰ ፣ እንጂ ፣ በዚህ ፣ አልዘገየም ። ሲሄድም ፣ ጄኔራል ፣ ክሌበር ፣ የተባለውን ፣ ለፈረንሳይ ፣ ጦር ፣ ጠቅላይ ፣ አድርጎት ፣ ሄደ ።

፩ ፤ ጄኔራል ፣ ክሌበር ፣ ጀግና ፣ ሰው ነበር ። ዳሩ ፣ ግን ጨካኝ ፣ ነበርና ፣ ጨካኝነቱ ፣ ሕይወቱን ፣ እስከ ፣ ማጣት ፣ አደረሰው ።

፭ ፤ ይኸው ፣ ጨካኙ ፣ ጄኔራል ፣ አንድ ፣ ቀን ፣ ሼህ ፣ ሳዳ ፣ የሚባል ፣ አንድ ፣ ሽማግሌ ፣ እስላም ፣ አገኘና ፣ ውስጥ ፣ እግሩን ፣ በከዘራ ፣ አስደበደበው ። ወዲያው ፣ ትንሽ ፣ እንደ ፣ ቈየ ፣ ጄኔራሉ ፣ ወደ ፣ መስጊድ ፣ ገብቶ ፣ ሳለ ፣ አንድ ፣ የተናደደ ፣ እስላም ፣ ገሥገሥና ፣ በጩቤ ፣ ቢሸጉበት ፣ ያን ፣ ጊዜውኑ ፣ ሞተ ።

፮ ፤ በ፲፰፻፩ ፣ ዓመት ፣ እንግሊዝ ፣ ፈረንሳዮችን ፣ ከግብፅ ፣ ለማስወጣት ፣ ከብዙ ፣ ጦር ፣ ጋራ ፣ ሰር ፣ ራልፍ ፣ አቤርክሮምቢን ፣ ሰደደው ። ጄኔራል ፣ መኑ ፣ የፈረንሳይ ፣ ኮማንደር ፣ ነበር ። አቡኬር ፣ ላይ ፣ ተዋጉና ፣ ሰር ፣ ራልፍ ፣ አቤርክሮምቢ ፣ ድል ፣ አደረገው ። ዳሩ ፣ ግን ፣ እርሱም ፣ ራሱ ፣ ክፉኛ ፣ ቈስሎ ፣ ነበር ።

፯ ፤ በዚያው ፣ ዓመት ፣ የፈረንሳይ ፣ ጦር ፣ ተሸነፈና ፣ ከግብፅ ፣ ወጥቶ ፣ በመርከብ ፣ ተሳፍሮ ፣ ወደ ፣ ፈረንሳይ ፣ አገር ፣ ተመለሰ ። ዳሩ ፣ ግን ፣ ባላገሮቹ ፣ ከፊተኞቹ ፣ ገዢዎቻቸው ፣ ከቱርኮች ፣ ይልቅ ፣ የፈረንሳይ ፣ ጄኔራል ፣ ቅን ፣ ፍርድ ፣ እየፈረደ ፣ በመልካም ፣ አገዛዝ ፣ በደንብና ፣ በሕግ ፣ ይገዛቸው ፣ ነበርና ፣ በመሄዱ ፣ እጅግ ፣ አዝነው ፣ ተላቀሱ ።

፰ ፤ የዛሬው ፣ የግብፅ ፣ ዋና ፣ ከተማ ፣ ትልቁ ፣ ካይሮ ፣ ነው ። ቀድሞ ፣ ከነበረው ፣ ይልቅ ፣ የዛሬው ፣ በጣም ፣ ትንሽ ፣ ነው ። ነገር ፣ ግን ፣ ፫፻ ፣ ሺሕ ፣ ባላገሮች ፣ ይኖሩበታል ። ፊት ፣ እንደ ፣ ተናገርሁ ፣ የእስክንድርያ ፣ ከተማ ፣ ትልቁ ፣ እስክንድር ፣ ከመሠረተው ፣ ያሁኑ ፣ ከጥንቱ ፣ በጣም ፣ ያንሳል ። ነገር ፣ ግን ፣ በዙሪያው ፣ ያለውን ፣ ፍራሹን ፣ ሲመለከቱት ፣ የጥንቱ ፣ ታላቅ ፣ እንደ ፣ ነበረ ፣ ይታወቃል ።

በማናቸውም ፣ የዓለም ፣ ክፍል ፣ ቢሆን ፣ ለመንገደኞች ፣ ፍዝዝ ፣ ያለ ፣ መስሎ ፣ የሚታይ ፣ እንደ ፣ ግብፅ ፣ የለም ። ባለፈው ፣ ዘመን ፣ የነበረውን ፣ ሀብትና ፣ የሚታየውንም ፣ ጌጥና ፣ ሽልማት ፣ ሲናገሩ ፣ በቀድሞው ፣ ከተማ ፣ መኻከልም ፣ ያሉት ፣ መንደሮችና ፣ ከተሞች ፣ ፍራሽ ፣ የዛሬውን ፣ የድኅነት ፣ መልክ ፣ ያሳያል ።

## ጥ ያ ቄ ።

፩ ፤ ተክሌዎፓትራ ፣ ሞት ፣ ጀምሮ ፣ ሜምሉኮች ፣ እስኪገዙት ፣ ድረስ ፣ የግብፅ ፣ አኗኗር ፣ እንዴት ፣ ሆነ ፣ ?

፪ ፤ ሜምሉኮች ፣ ግብፅን ፣ ስንት ፣ ዘመን ፣ ገዙት ፣ ? ቱርኮች ፣ ግብፅን ፣ ስንት ፣ ዓመት ፣ ገዙት ፣ ? የገዙበት ፣ ዘመን ፣ ምን ፣ ጊዜ ፣ ነው ፣ ? በ፲፯፻፺፰ ፣ ምን ፣ ተደረገ ፣ ?

፫ ፤ እንዴት ፣ ያለ ፣ ጦርነት ፣ ተደረገ ፣ ? ከድሉ ፣ በኋላ ፣ ቦናፓርቴ ፣ ምን ፣ ሆነ ፣ ?

፬ ፤ ጀኔራል ፡ ኬልበር ፡ ምን ፡ ሆነ ፡ ?

፭ ፤ ባ፲፰፻፩ ፡ ምን ፡ ሆነ ፡ ?

፮ ፤ በዚያው ፡ ዘመን ፡ ምን ፡ ተደረገ ፡ ? ፈረንሳይ ፡ ግብፆችን ፡ ቢተዋቸው ፡ ለምን ፡ አዘኑ ፡ ? አሁን ፡ ግብፅ ፡ የሚገዛው ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ? አገሩ ፡ እንደምን ፡ ይታሰባል ፡ ?

፯ ፤ የግብፅ ፡ ዋናው ፡ ከተማ ፡ የትኛው ፡ ነው ፡ ? ታላቁ ፡ ካይሮ ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ? የሕዝቡ ፡ ብዛት ፡ ስንት ፡ ይሆን ፡ ? እስክንድርያ ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ? ግብፅ ፡ ለመንገደኞች ፡ ምን ፡ መስሎ ፡ ይታያቸዋል ፡ ?